# የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን

## 1993 የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናት የኢዲቲንግ እና ኮዲንግ መመሪያ

( EDITING AND CODINING MANUAL )

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 1993 ዓ.ም.

# ማ ው ጫ

ገጽ


ምዕራፍ 1

መግቢያ ---------- 1

ምዕራፍ 2 አጠቃላይ መመሪያ ---------- 1

ምዕራፍ 3 በቅጽ 1 የቤተሰብ መጠይቅን ማረም ---------- 2

ክፍል 1 የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ/ዓምድ 1-11/ ---------- 2
ክፍል 2 ስለ ቤተሰቡ መደበኛ አባላት ዝርዝር መረጃዎች/ከዓምድ 12-23/ ---------- 3
ክፍል 3 ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ (ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ) ---------- 5
ክፍል 4 ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ) ---------- 9

ምዕራፍ 4 ቅጽ 1 ክፍል 5- ስለቤተሰቡና ቤተሰቡ ስለሚኖርበት ቤት ዝርዝር መረጃ መጠይቅን ማረም ---------- 10

ምዕራፍ 5 የቅጽ 2- ዕድሜአቸው ከ 5-17 ዓመት ስለሆኑ ልጆች የሥራ ስምሪት ሁኔታ መጠይቅን ማረም ---------- 12

ክፍል 1 የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ/ዓምድ 1-11/ ---------- 12
ክፍል 6 የልጆች የፍልሰት ሁኔታ ---------- 13
ክፍል 7 የልጆች የትምህርት ሁኔታ ---------- 13
ክፍል 8 ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ሁኔታና ምንም አለመሥራት ---------- 14
ክፍል 9 ባለፍት በማናቸውም ጊዜያት በሥራ ላይ ተሰማርተው የማያውቁ ልጆች ከሰሩት ወይም ከሚሰሩት ስራ ጋር በተያያዘ የጤናና የደህንነት ሁኔታን የተመለከቱ ጥያቄዎች ---------- 15
ክፍል 10 ቤተሰብ/አሳዳጊ ላልሆነ ለሌላ ሰው በክፍያ (በገንዘብ ወይም በዓይነት) ወይም ያለክፍያ ተቀጥረው ስለሚሠሩ ልጆች ---------- 16
ክፍል 11 በምርታማ ሥራ የተሠማሩ ልጆች በመደበኛነት የሚኖሩባቸው ወላጆች (አሳዳጊዎች) ስለ ልጆቹ ያላቸው አመለካከት ---------- 17

ምዕራፍ 6 የቅጽ 3 ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት ስለሆኑ ልጆች የሥራ ስምሪት ሁኔታ መጠይቅን ማረም ---------- 18

ክፍል 12 ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆች የትምህርት፣ የሥራ ሁኔታና በስራ ላይ ስለሚደርሱ ጉዳቶችና ህመሞች ---------- 18
ዕዝል 1 የዋና ዋና ብሔረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር ---------- 24
ዕዝል 2 የዞኖች ስምና ኮድ ዝርዝር ---------- 26

# የ1993 የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

# (Editing and Coding Manual)

## ምዕራፍ I

## መግቢያ

በተለያዩ የአለም ክፍሎች ልጆች የሥራ ዕድሜአቸው ከመድረሱ አስቀድሞ የአካልና የአዕምሮ ዕድገታቸውን በሚጎዱ ከባድ ሥራዎች እንደሚሠሩ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ ። በታዳጊ አገሮች ልጆች ከቤት ውስጥ ሥራ አንስቶ በተለያዩ ቀላልና ከባድ የሥራ መስኮች እንደሚሠማሩ ይታወቃል። የልጆች የሥራ ሥምሪት መረጃዎች የልጆችን የትምህርት፣ የጤናና ሥራ ሁኔታን አስመልክቶ ለሚነደፉ ዕቅዶች ስለሚጠቅሙና ለአፈፃፀም ክትትል ስለሚያስፈልጉ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን በመጋቢት 1993 አገር አቀፍ የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት በማድረግ መረጃ ሰብስቧል። ጥናቱ ግቡን እንዲመታ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ስራዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድ ሰጥቶ ለሚቀጥለው የሥራ ክፍል ማስተላለፍ ነው። ስለሆነም የኮድ አሰጣጥና ዕርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል። በተለይም በዚህ ጥናት ከተካተቱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህንም ጥያቄዎች እርስ በርስ ለማመሳከር ከሚፈጥረው ውስብስብ አሠራር አኳያ አራሚው ስለ ጥናቱ መረጃ አሰባሰብ በቂ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። በተጨማሪ የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም የአገልግሎት መረጃ ኮድ ሲደረግ በመጠይቁ የተሞሉትን መረጃዎች በጥሞናና በእርጋታ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል። ስለሆነም በመጠይቁ እርማትና ኮድ መስጠት ሥራ የሚሳተፉ ሠራተኞች የጥናቱን ውጤት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ የሥራ ድረሻ የተጣለባቸው መሆኑን አውቀው የእርማትና ኮድ አሰጣጡን መመሪያ በደንብ መረዳት ይጠበቅባቸዋል።

## ምዕራፍ II

## አጠቃላይ መመሪያ

1. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል። አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ ያስፈልጋል።
2. ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ በትክክል ተሞልቶ መምጣቱንና አረጋግጦ መረከብ ያስፈልጋል። በአንድ ቆጠራ ቦታ ለ35 ቤተሰቦች መረጃ የተሞላላቸው ሲሆን ለእያንዳንዱ ቤተሰብም አንድ ባለ 6 ገጽ ቅጽ 1 (A 3 size) እና 1 ባለ 1 ገጽ አባሪ መጠይቅ ይኖሩታል። በተጨማሪም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ለሆናቸው ልጆች ለእያንዳንዳቸው ቅጽ 2 ( 3 ገጽ) እና ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት ለሆኑ ልጆች ለእያንዳንዳቸው ቅጽ 3 (ባለ 3 ገጽ) መሞላቱን ማረጋጥ ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡ አስተያየቶችን በሚገባ መያያዛቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው።
3. እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢው ያሰፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም። መረጃው እርማት የሚደረግበት ከሆነ ከሰፈረው መረጃ አጠገብ መረጃው ከተጻፈበት ቀለም በተለየ ቀለም እርማቱ ይደረጋል።

4. አንዳንድ አስተያየት የተሰጠባቸው መረጃዎች በእርማቱና በኮድ አሰጣጡ ወቅት ልዩ ጥንቃቄ የሚሹ ስለሆነ ከመታረሙ በፊት ተቆጣጣሪውን ማሳየት እና እርሱ በሰጠው ውሣኔ መሠረት መከናወን አለበት::

5. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ ጽሕፈቱ በሚነበብ ሁኔታና በንጽህና መሠራት አለበት::

6. በእያንዳንዱ ዓምድ ኮድ ለማስፈር በተሠሩ ካርድ ኮለሞች ኮድ የተሞላባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በእርግጥ እንደሁኔታው በተለይ የሚዘለሉ ዓምዶች በካርድ ኮለሙ (....) ይሞላል:: በተለይ መረጃው የሚቀነባበረው በኮምፒውተር ስለሆነ መረጃውና የጥናቱ ትንተና ዘዴዎች የሚገናኙት በኮድ አማካይነት ብቻ ስለሆነ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሠራት አለበት::

7. የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ ባልተሞላባቸው መጠይቆች ሁሉ ቤተሰቡ በሚኖርበት የቆጠራ ቦታ ከሚኖሩ ሌሎች ቤተሰቦች መጠይቆች በማየት ይሞላል::

8. ለአንድ ቤተሰብ ከተሞላው የመጠይቆች ጥራዝ የተነጣጠሉ መጠይቆች ካጋጠሙ የአድራሻ መለያውን በመጠቀም በአንድ ላይ ማድረግና መስፋት ያስፈልጋል::

9. በየአምዱ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተዘረዘሩት አማራጮች (ለምሣሌ:- አዎን/የለም) መረጃ ሰብሳቢው በየዓምዱ የሞላው መልስ በካርድ ኮለሙ/ኮለሞቹ ከተሞሉት ኮዶች ጋር የሚገናዘቡ መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል::

10. በአንድ ካርድ ኮለም ከአንድ ቁጥር በላይ መጻፍ ስለሌለበት ይህ በሚያጋጥምበት ሁሉ ተገቢው ዕርማት ይደረጋል::

11. ቁጥሮቹ በካርድ ኮለሞች በሚጻፉበት ጊዜ ከቀኝ ወደ ግራ መሆን ስለሚገባቸው በትክክል መከናወኑን ማየትና ማረም::

12. በዚህ ጥናት መጠይቅ ውስጥ ብዙዎቹ አምዶች/ጥያቄዎች ውስጥ «ወደ ዓምድ/ጥያቄ __ ይለፉ» የሚሉ ትዕዛዞች ስላሉ ወደተባሉት አምዶች መተላለፋቸውን በጥንቃቄ ማገናዘብ ያስፈልጋል:: የይለፍ ሕግ ያላቸው አማራጭ ኮዶች በሙሉ ከጎናቸው የቀስት ምልክት ሲኖራቸው ነገር ግን ከጎናቸው ቀስት የሌላቸው ምንም አምድ/ጥያቄ ሳይዘለልላቸው በቀጥታ ቀጥሎ ያለው አምድ/ጥያቄ የሚጠየቅላቸው ናቸው:: እንዲሁም «ሁሉም ወደ ዓምድ ______ ይለፍ» የሚል ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ ይህ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ዓምድ የተጠየቁ ሰዎች በሙሉ እንዲታለፍ ከተፈለገው ዓምድ በፊት ያሉትን ጥያቄዎች አይጠየቁም:: ሌላው ነገር አባሪ መጠይቅ ነጠላ ስለሆነ እንዳይጠፉ ወረቀቱን በቅፅ 1 ገፅ 5 አናት በስተቀኝ ጫፍ ላይ በስቴፕለር ማያያዝ አለብን::

## ምዕራፍ III

## <u>ቅጽ 1 የቤተሰብ አባላት መጠይቅን ማረም</u>

<u>ክፍል 1:-</u> <u>የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ</u>
ከዓምድ 2 እስከ ዓምድ 8 ያለውን የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ (ከተማ፣ ከፍተኛ) ቀበሌ/ገበሬ ማኅበር ስሞች እና የቆጠራ ቦታ በትክክል መሰጠቱን በማገናዘብ ማስተካከል ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከክልል እስከ ቀበሌ/ገበሬ ማህበር ላሉት ዓምዶች ካርድ ኮለሞቹ መስክ ላይ ያልተሞሉ ስለሆነ በእዝል የቀረበውን የአካባቢ መለያ ኮድ በመጠቀም ካርድ ኮለሞቹን መሙላት ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 2-4:</u> <u>ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ:-</u> ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ፣ በትክክል መሞላቱ መረጋገጥ አለበት:: በካርድ ኮለሞቹ ተስማሚው ኮድ ይሞላል::

<u>ዓምድ 5:-</u> <u>ከተማ:-</u> ለከተማው ጥናት የከተማው ስም በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል:: ለገጠሩ ጥናት ይህ ዓምድ ኮድ 8 ይሞላል::

<u>ዓምድ 6:-</u> <u>ከፍተኛ/ወረዳ:-</u> ጥናቱ በከተማ የሚካሄድ ከሆነ የከፍተኛው ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በካርድ ኮለሞቹ ... ጥናቱ በገጠር የሚካሄድ ከሆነ ኮድ 8 ይሞላል::

ዓምድ 7:- ቀበሌ/ገበሬ ማኅበር:- በከተማ የቀበሌው ስም፣ በገጠር ደግሞ የገበሬ ማኅበሩ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ እና በካርድ ኮለሞቹ የቀበሌው ወይም የገበሬ ማኅበሩ ኮድ በትክክል ይሞላል::

ዓምድ 8:- የቆጠራ ቦታ:- የቆጠራ ቦታ ኮድ በካርድ ኮለሞቹ በትክክል መሞላቱን ማጤን ያስፈልጋል::

ዓምድ 9:- የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር:- በአንድ የቆጠራ ቦታ ለጥናቱ የሚመረጡ ቤተሰቦች በጠቅላላ ብዛት 35 ነው:: በዚህ ዓምድ ባሉት በካርድ ኮለም የተሞላው ቁጥር ከ01 - 35 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 10:- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም:- በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም መፃፉን እንዲሁም በክፍል 2 ዓምድ 11 በመጀመሪያ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ባይሆን ግን ተቆጣጣሪው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል::

ዓምድ 11:- የመልስ ሰጪ የመስመር ቁጥር :- በዚህ ዓምድ ባሉት ካርድ ኮለሞች የሚሞላው ከቤተሰቡ አባላት ውስጥ ለጥያቄዎቹ መልስ የሰጠው ግለሰብ የመስመር ቁጥር ነው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ ባሉት ካርድ ኮለሞች የሚሞላው ቁጥር የቤተሰቡን አባላት ብዛት ከሚገልነው ቁጥር ሊበልጥ አይችልም::

## ክፍል 2: ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ

ከዓምድ 12-18 ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ዓምድ 12:- ተራ ቁጥር:- ይህ ከ01 በመጀመር በተከታታይ ቁጥር የተሰጠበት ስለሆነ ምንም አይነካም:: ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስከ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል:: 12 አባላት ላሉት ቤተሰብ የ12ኛው አባል መረጃ ሌላ መጠይቅ መጠቀም ሳያስፈልግ እዛው መጠይቅ ግርጌ ከ11ኛው አባል በመቀጠል ሊሞላ ስለሚችል አራሚዎች በሥራቸው ወቅት ይህን ማስተዋል አለባቸው::

ዓምድ 13:- የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም:-
የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም::

ዓምድ 14:- ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና:- በዚህ ዓምድ ሥር ባለው ንዑስ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት የኮድ ቁጥሮች ከ01-12 ያሉ ብቻ ናቸው:: አባላቱ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚገልጽበት ኮዶች እና የተሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ እና የማይዛመድ ከሆነ ኮዱን ማስተካከል ያስፈልጋል:: የኮዶቹ ዝርዝርና መግለጫቸው ከጥያቄው ሥር ይገኛል::

ዓምድ 15:- ጾታ:- በዚህ ዓምድ ባለው ክፍት ቦታ መታየት ያለባቸው 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው:: ስለ ኮዱ ትክክለኛነት በዓምዱ ሥር በተሰጠው ቦታ የሰፈረውን የጾታ መለያ ማየት ያስፈልጋል:: ሆኖም መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የግለሰቡን ጾታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል:: ኮድ 9 አይፈቀድም:: ፆታ ካልተፃፈ ስም ታይቶ ይሞላል:: ይህም ካልተቻለ በግምት ይሞላል::

ዓምድ 16:- ዕድሜ:- ይህ ዓምድ መስክ ላይ ተሞልቶ የሚመጣ ነው:: ሆኖም በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ "97" ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል:: ኮድ 99 አይፈቀድም ዕድሜ ካልተፃፈ ዝምድናና የልጆች ዕድሜ፣ የባል ዕድሜ ታይቶ በግምት ይሞላል:: በተጨማሪም የዕድሜ መረጃ ካልተሞላ የቤተሰብ አመዘጋገብ ቅደም ተከተልና በዕድሜ ከተገደቡ ዓምዶች ለግለሰቡ የተሞሉ መረጃዎችን በማመሳከር መረጃውን ለመሙላት ይሞከር:: ይኸውም ሲሆን ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር የሚፈፀም ይሆናል::

ዓምድ 17:- ሃይማኖት:- በዚህ ዓምድ ባለው ንዑስ ዓምድ ላይ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-6 ብቻ መሆን አለባቸው:: ከነኚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ ቁጥር ተሞልቶ ከመጣ ሁኔታውን ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ማስተካከል ተገቢ ነው:: የሃይማኖት ኮድ ተሞልቶ ካልመጣ፣ ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ የወላጆቻቸው (የኃላፊው) ሃይማኖት እንደሚከተሉ በማሰብ ተገቢው ኮድ ይሞላል:: ይህም የሚሆነው ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር ነው::

ዓምድ 18:- ብሔረሰብ:- ለሁሉም የቤተሰብ አባል ከላይ ባለው ክፍት ቦታ የብሔረሰቡም ስም ከብሔረሰቡ ስር በሚገኙት ንዑስ ዓምዶች ደግሞ የብሔረሰቡ ኮድ በትክክል መጻፋቸውን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: የብሔረሰቦችን ኮድ ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ዕዝል 1 ውስጥ ይመልከቱ:: የአንድ ቤተሰብ አባል የብሔረሰብ ዓምድ ካልተሞላ፣ ዕድሜው ከ18 በታች ከሆነ የኃላፊው ብሔረሰብ ይሰጠዋል:: ይህም ሲሆን ከተቆጣጣሪው ጋር መመካከር ያስፈልጋል::

ዓምድ 19-27:- የትምህርት ሁኔታ (ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

እ'ኚህ ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ ስለሆነ ከ5 ዓመት በታች ለሆነ ልጅ መረጃ ተሞልቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ በማሳወቅ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ግለሰብ መረጃ ሳይሞላለት ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ተገቢውን ኮድ መሙላት ተገቢ ነው::

ዓምድ 19:- ማንበብና መጻፍ ይችላሉ :-ይህ ዓምድ 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መጻፍ መቻላቸው ተጠይቆ «አዎን» ለመለሱ ኮድ 1 «የለም» ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላበት ነው:: ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የሚመጡት ቁጥሮች ከ1 ወይም ከ2 ውጭ መሆን የለባቸውም:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓምድ (ዓምድ 20) ላይ ከተሞላው መረጃ በመነሳት ማስተካከል ስለሚቻል አዲተሩ ለተቆጣጣሪው ማማከር አለበት::

ዓምድ 20: የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?:- በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ መረጃ የሚሞላው በዓምድ 19 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ በዓምድ 19 ኮድ 2 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ምንም ዓይነት መረጃ እንዳልተሞላ ማረጋገጥ ተሞልቶም ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር መረጃውን መሰረዝ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ቀጥሎም ከላይ ባለው በዓምዱ ክፍት ቦታ የተጻፈው መረጃ ከሥር በካርድ ኮለሙ ውስጥ ከተፃፈው ኮድ ጋር መጣጣማቸውን ማገናዘብ ተገቢ ነው:: ለዚህም ከዚህ በታች ያሉትን ኮዶች መመልከት ያስፈልጋል::

ዓምድ 21-22:- የሥልጠና ሁኔታ (ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

በነኚህ ዓምዶች መረጃ የሚሞላላቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆነው የቤተሰብ አባል መረጃ ተሞልቶ አለመምጣቱኝ፣ በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ያሻል::

ዓምድ 21:- የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስደውና አጠናቀው የምስክር ወረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝተዋል?:-በዚህ ዓምድ በሚገኘው ካርድ ኮለም አዎን ለመለሱ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥለውን ዓምድ ማለትም ዓምድ 22 ሳይሞላላቸው በሰረዝ ታልፈው ወደ ዓምድ 23 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በዓምድ 22 ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ መሙላት ይቻላል:: ይህም ሲደረግ ተቆጣጣሪው ማየት አለበት::

ዓምድ 22:- የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነት ምንድ ነው?:-በዓምድ 21 የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስጄና አጠናቅቄ የምስክር ወረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነትና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሙያ ዓይነቶቹንና ተገቢውን ኮድ ለማገናዘብ ከታች የቀረበውን ዝርዝር ይመልከቱ::

01= ሽክላ ስራ
02= ሽመና
03= እንጨት ሥራ (የአናጢነት ስልጠናን ይጨምራል)
04= ኤሌክትሪክ ሥራ
05= ብረታ ብረት
06= መካኒክ (የመኪና፣ የሞተር ሳይክል፣ የአውሮፕላን ጥገናን ይጨምራል)
07= ግንበኝነት
08= ታይፐ
09= ልብስ ስፌት
10= ሹፌርነት
11= የልማት ተጠሪ /DA/
12= ልምድ አዋላጅ
13= ኮምፒውተር ሳይንስ (ፐሮግራመር)
14= ኮምፒውተር አጠቃቀም
15= በግብርና አነስተኛ ስልጠና ሙያ (ከአጋርፍ፣ አርዳይታ ባኮ፣ ወዘተ)
16= ሆቴልና ቱሪዝም
17= ፖሊስ
18= መምህርነት (ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ ከቴክኒክማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ ከመምህራን ማሰልጠኛተቋም፣)
19= ውትድርና
20= ሌላ (ይገለጽ)

<u>ዓምድ 23:-</u> <u>የጋብቻ ሁኔታ</u> (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ):- ይህ ዓምድ እንደ «ሥልጠና ሁኔታ» የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ሳይሞላ መምጣቱን፤ በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ተገቢ ነው:: በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከኮድ 1-5 ከተዘረዘሩት ውጭ እንዳልሆነ ማየት ያስፈልጋል::

## <u>ክፍል 3:-</u> <u>ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ</u>

<u>ማስታወሻ:-</u> የክፍል 3 እርማት ከመደረጉ በፊት በገጽ 2 ከክፍል 3 በላይ ያለው የአካባቢ መለያ (ክፍል 1) ከገጽ 1 ክፍል 1 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 13:-</u> <u>መሉ ስም:-</u> ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 13 በቀጥታ የሚወራረስ ነው:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 13 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል:: በተለይም የስሞች አመዘጋገብ በሁሉም ገጾች በተመሳሳይ ቅደም ተከተል መሆኑ መረጋገጥ አለበት:: ይኸም የሚያስፈልገው መረጃ አግድም Key ስለሚደረግ የአንዱ መረጃ ለሌላው እንዳይፃፍ ነው::

<u>ዓምድ 12:-</u> <u>የመስመር ቁጥር:-</u>ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም:: ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስከ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 16:-</u> <u>ዕድሜ:-</u> ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 16 በቀጥታ የሚወራረስ ነው::

## <u>ዓምድ 24-43 ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሥምሪት ሁኔታ</u>

<u>ዓምድ 24:-</u> ይህ ጥያቄ ከዚህ በኃላ ለሚመጡ ጥያቄዎችና ክፍሎች መነሻና መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ በጥንቃቄ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለሆነም ከላይ ከተዘረዘሩት ምርታማ ሥራዎች ቢያንስ በአንዱ ለተሰማራ የቤተሰብ አባል «አዎን» የሚለው ኮድ 1 መሞላቱን በአንፃሩም በአንዱም እንኳን ላልተሰማራ «የለም» የሚለው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለዚህ በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም «የለም» መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዮ ዓምድ 25 መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

<u>ዓምድ 25:-</u> ይህንን ዓምድ የሚጠየቁት ዓምድ 24 ላይ ኮድ 2 የተሞላላቸው ብቻ ስለሆኑ ከዓምድ 24 ኮድ 1 የተሞላላቸው እዚህ ዓምድ ላይ ምንም ሳይጠየቁ በሰረዝ መታለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 26:- የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሠሯቸው በሁሉም ስራዎችዎ ለስንት ሰዓት ሰርተዋል? :- ይህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት በጠቅላላው የተሰራ የሥራ ሰዓት መጠን መመዝገቢያ ነው:: እንደ ዓምድ 24 ሁሉ ይህም ዓምድ መሠረታዊ ነው:: ምክንያቱም በሳምንት ውስጥ በሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ላይ ተመርኩዘን የቤተሰብ አባላትን ሥራ ያላቸው፣ ሥራ አጥ ወይም ከሁለቱም ውጭ ለመከፋፈል ለመከፈል ስለሚረዳን ነው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ ያሉት መረጃዎች በጥንቃቄ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ሳምንት ሥራ ሰዓት ድምር «97» እና ከዛ በላይ ከሆነ «የሳምንቱ ድምር» በሚለው ንዑስ ዓምድ ሥር መታየት ያለበት ቁጥር «97» ነው:: ይህ ካልሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን ማስተካከል ያስፈልጋል:: በተቻለ መጠን በነዚህ ዓምዶች ኮድ 99 እንዳይሰፍር ይፈልጋል::

ዓምድ 27:- በዓምድ 26 ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር?:- ለዚህ ጥያቄ በመጠይቁ ላይ የቀረቡት አማራጮች 2 ሲሆኑ እነዚህም 1. 4 ሰዓትና በላይ፤ 2. ከ4 ሰዓት በታች የሚሉ ናቸው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ኮድ «1» ወይም ኮድ «2» ብቻ መሆን አለበት:: ከዚያም ከ4 ሰዓት በላይ ሰርተው ኮድ «1» የተሞላላቸው ቀጣዩን አምድ ማለትም አምድ 28ን ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 29 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 28:- ሥራ እያለዎ ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?:-መጀመሪያ ይህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶ የሚመጣው በዓምድ 27 ኮድ «2» ለተሞላላቸው ማለትም በአጠቃላይ በሳምንት ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ለሆነ የቤተሰብ አባላት እና ባለፈው 7 ቀናት በስራ ላይ ላልተሰማሩ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ስለዚህ ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ የቤተሰብ አባላት ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተሠማሩ አዎን የሚለው ኮድ «1-3» ሲሞላ ነገር ግን ሥራ ሳይኖራቸው ከሆነ የለም የሚለው ኮድ «4» ሊሞላላቸው ይገባል:: በመጨረሻም በዚህ ዓምድ የለም ብለው ኮድ «4» የተሞላላቸው ግለሰቦች እስከ ዓምድ 43 ድረስ ምንም መረጃ ሳይሞላላቸው በቀጥታ ወደ ዓምድ 44 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 29:- የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድን ነው? :- በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ «የሥራ ዓይነት የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር» ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ይሞላል:: በካርድ ኮለሞቹ ኮድ ከመሞላቱ በፊት በዓምድ 30 ስለሥራው ዓይነት የተሰጠውን ዝርዝር ማየት ይገባል:: የዋነኛ የሥራ ዓይነቱን ከኮድ ዝርዝሩ መጽሐፍ ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልጽና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ የሆነ ሊያጋጥም ስለሚችል ኢዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ሰብሳቢው የሞላውን መረጃ ማጣራት ይኖርበታል:: ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞከር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዝርዝር በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተቻኩሎ ኮድ ከማድረግ በመቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ይገባል:: በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማይገጥም ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል::

ዓምድ 30:- በዋነኛነት ያከናወኑት ሥራ በዝርዝር ይግለፁልኝ :- ይህ ጥያቄ በዓምድ 29 ኮድ ለመስጠት አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥር አንዳንድ የሥራ ዓይነቶችን ግልፅ የሆነ እርማት ለማድረግ ይጠቅማል:: ስለዚህ በዓምድ 29 የሚያስቸግር የሥራ ዓይነት ሲያጋጥም ይህንን ዓምድ አገናዝቦ ኮድ መስጠት ያስፈልጋል::

ዓምድ 31:- በዋነኝነት የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድ ነው? በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ ሳምንት በሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ በዋነኝነት የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት /ኢንዱስትሪ/ ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ የኢንዱስትሪ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ ከ«የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ዝርዝር» ተብሎ የተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ይሞላል:: የኢንዱስትሪ ዓይነቱን ከኮድ ዝርዝሩ መጽሐፍ ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የኢንዱስትሪ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: በመስክ ላይ የተሞላው የድርጅቱ

ምርት/አገልግሎት ሳይሆን የድርጅቱ ስም ወይም ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል:: በዚህን ጊዜ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት ምን እንደሆነ ለማወቅ መጣሬ ያስፈልጋል::

ዓምድ 32:- <u>በዋነኛነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት/አገልግሎት ዓይነት በዝርዝር ይግለፁልኝ?</u>:- ይህም ዓምድ ልክ እንደ ዓምድ 30 የድርጅት ዋና ምርት/አገልግሎት ዝርዝር መግለጫ ስለሆነ እዚህ በዝርዝር የሚገለፀው የድርጅት ምርት/አገልግሎት ለዓምድ 31 ግልፅ የሆነ ኮድ ለመስጠት ስለሚረዳ እንደማገናዘቢያ መገልገል ይገባናል::

ማስታወሻ:- የዓምድ 33 እና ዓምድ 45 እርማት ከመደረጉ በፊት በገጽ 3 ያለው አካባቢ መለያ (ክፍል 1) ከገጽ 1 ክፍል 1 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 13:-<u>መሉ ስም:</u>- ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 13 በቀጥታ የሚወራረስ ነው:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 13 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል:: በተለይም የስሞች አመዘጋገብ በሁሉም ገጾች በተመሳሳይ ቅደም ተከተል መሆኑ መረጋገጥ አለበት:: ይኸም የሚያስፈልገው መረጃ አግድም Key ስለሚደረግ የአንዱ መረጃ ለሌላው እንዳይፃፍ ነው::

ዓምድ 12:- <u>የመስመር ቁጥር:</u>- ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም:: ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 16:-</u> <u>ዕድሜ:</u>- ይህ ዓምድ ገፅ 1 ዓምድ 16 በቀጥታ የሚወራረስ ነው::

ዓምድ 33:- <u>የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ ምንድን ነው?:-</u> ለዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የቅጥር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት 8 አማራጭ መልሶች ከኮድ 1-8 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከኮድ 3-8 የተሞላላቸው የቤተሰቡ አባላት እስከ ዓምድ 38 ሳይጠየቁ በቀጥታ ወደ ዓምድ 39 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: የየአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል::

ዓምድ 34:- <u>ለሥራዎ በምን ያህል ጊዜ ይከፈልዎታል?:-</u> ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በዓምድ 33 ኮድ 1 ወይም 2 ለተሞላላቸው ብቻ በመሆኑ ከኮድ 3-8 የተሞላላቸው እዚህ ዓምድ ውስጥ ከተሞላላቸው መስተካከል ስለሚገባው ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚህ ዓምድ ያሉት አማራጮች ከኮድ 1-7 ስለሆነ ከዚህ ቁጥር ውጭ ከተሞላ ለተቆጣጣሪው በማሳየት መፍትሄ ማግኘት ይገባል:: የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል::

ዓምድ 35:- <u>ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት ወይስ በሁለቱም?:-</u>ለዚህ ጥያቄ ሦስት አማራጭ መልሶች ብቻ ተዘርዝረዋል:: ስለዚህ ከኮድ 1-3 ካሉት ቁጥሮች መካከል አንዱ ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል:: የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል::

*ዓምድ 36-38 :- <u>በቅርቡ ለሠሩት ሥራ በመጨረሻው ክፍያ ምን ያህል ተከፈለዎት?</u>*

<u>ዓምድ 36</u>:- <u>ክፍያ በገንዘብ:-</u>እዚህ ዓምድ የተሞላው የሰራተኛው የክፍያ ስምምነት በገንዘብ የሆነ ከሆነ የገንዘቡ መጠን ይፃፋል:: ነገር ግን ሠራተኛው በገንዘብ የማይከፈለው ከሆነ ኮድ «0000» የተሞላ ይሆናል:: ነገር ግን መረጃ ሰብሳቢዎች «0000» ከመሙላት ይልቅ «--» ስለሚያደርጉ ይህንን ማስተካከል ተገቢ ነው:: በሌላ መልኩ ደግሞ ሠራተኛው በገንዘብ ተቀጥሮ ነገር ግን እስካሁን ያልተከፈለው ከሆነ ኮድ «9998» የተሞላለት ይሆናል:: እዚህ ላይ «9997» በላይ የሚከፈላቸው ደግሞ «9997» ተብሎ የተሞላ ይሆናል::

ዓምድ 37:- <u>ክፍያ በአይነት:-</u> በዚህ ዓምድ የተሞላውም በዓምድ 36 ጋር ተመሣሣይነት ያለው ነው:: ስለሆነም ክፍያ በአይነት የሚቀበል ሠራተኛ ወደ ገንዘብ የተተመነለት ስለሆነ የገንዘቡ ልክ እዚህ ዓምድ ላይ ይፃፋል:: እንደ ዓምድ 36 ሁሉ ለዓይነት ክፍያ የማያገኙ ኮድ «0000» የተሞላላቸው ሲሆኑ ኮድ «9998» የተሞላላቸው ደግሞ

ክፍያ በዓይነት ተስማምተው ነገር ግን እስካሁን ያለተከፈላቸው ናቸው:: ኮድ «9997» የተሞላው ደግሞ «9997» እና በላይ ክፍያ ለሚያገኙ ነው::

ዓምድ 38:- <u>በአጠቃላይ የተገኘ ገቢ:-</u> የዓምድ 36 እና የዓምድ 37 ድምር በዚህ ዓምድ በትክክል መደመሩን መፃፉን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በተጨማሪም ኮድ «9998» የተሞላላቸው ሰዎች ኮዱ እንደ ብር ተወስዶ ያለመደመሩን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በዓምድ 36 ኮድ «9998» እና በዓምድ 37 ይኸው ኮድ ቢሞላ ድምሩ ላይ መፃፍ ያለበት ያው 9998 እንጅ የሁለቱ ድምር ወይም «9997»ያለመሆኑን ማጤን ይገባል:: በሌላ መልኩ ደግሞ ዓምድ 36 ወይም በዓምድ 37 ኮድ 9998 ተሞልቶ ሌላኛው ዓምድ የተለየ ቁጥር ተሞልቶ ከሆነ በዓምድ 38 ላይ ይህ የተለየው ቁጥር ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ማስተካከል ይገባል::

*ዓምድ 39-40 :- <u>የሥራ ሰዓት ፈረቃ :-</u>*

በእነዚህ ዓምዶች የሚጠየቀው የሥራ ሰዓት ፈረቃ ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሰዎች ስለሆነ ከዚህ ዕድሜ በታች ተሞልቶ ከመጣ ልክ እንደሌሎቹ ዓምዶች ሁሉ ለተቆጣጣሪው በማሳየት ማስተካከል ያስፈልጋል::

ዓምድ 39:- <u>አብዛኛውን ጊዜ ቀን ወይም ምሽት/ሌሊት ይሠራሉ?:-</u> ለዚህ ዓምድ የተሰጡት አማራጮች ከ1-3 ስለሆኑ በካርድ ኮለሙ ውስጥ መታየት ያለባቸውም እነዚህ ቁጥሮች ብቻ ናቸው:: ስለዚህ ከዚህ ውጭ ቁጥር ከታየ መስተካከሉ ለሚቀጥለውም ዓምድ ጠቀሜታው የጎላ ነው::

ዓምድ 40 :- <u>አብዛኛውን ጊዜ - ለስንት ሰዓት ይሰራሉ?:-</u> ይህ ዓምድ የተሞላው ከዓምድ 39 ጋር እየተገናዘበ ስለሆነ የዓምድ 39 አማራጮችን ከፍተኛ ሰዓት ማወቅ ያስፈልጋል:: ይህም ማለት በዓምድ 39 ላይ ኮድ 1 የተሞላለት በዓምድ 40 ላይ ሰዓቱ ከ12 መብለጥ የለበትም:: እንዲሁም በዓምድ 39 ኮድ 3 የመለሰ በዚህ ዓምድ ከፍተኛው ሰዓት 24 ሰዓት ብቻ ይሆናል ማለት ነው::

*<u>ዓምድ 41-43:- ስለተጨማሪ ስራ/ስራ ስለመቀየር (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)</u>*

በነዚህ ዓምዶች መረጃ የሚጠየቅላቸው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ስለሆነ ይህንን ዓምድ ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በታች የሆኑ በስረዝ የታለፈላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል:: በተለይ ደግሞ እስከ ዓምድ 40 ድረስ ከ5 ዓመት በላይ የሆኑ ልጆች ስለሚጠየቁ እዚህ ዓምድ ውስጥ አለመግባታቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል::

ዓምድ 41:- <u>ባለፉት ሰባት ቀናት ይሰሩት ከነበረው ዋነኛ የሥራ ዓይነት በተደራቢነት ሌላ ምርታማ ሥራ ሠርተዋል?</u> ይህን ዓምድ የሚጠየቁት ወደዚህ ክፍል የመጡ ግለሰቦች ሁሉም ናቸው:: ለጥያቄውም መልስ የሚሰጠው ሁለት አማራጭ መልሶች ማለትም አዎን ብለው ለመለሱ ኮድ «1» የለም ላሉ ኮድ «2» በመሙላት ነው:: ስለሆነም በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡ ቁጥሮች ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 42:- <u>ባለፉት 7 ቀናት ይሰሩት ከነበረው ሥራ በተጨማሪ ሌላ ሥራ ለመሥራት ጥረት አድርገው ነበር? ወይም ለመሥራት ዝግጁ ነበሩ?:-</u> በዚህ ዓምድ መረጃ ሊሞላላቸው የሚገባ ግለሰቦች ዓምድ 41 ላይ የተጠየቁ ሲሆኑ ለዚህም ኮድ 1 ወይም 2 ሊሞላላቸው ይችላል:: ስለዚህ ይህም አምድ ያለው ሁለት አማራጭ ብቻ ስለሆነ «አዎን» ብለው ለመለሱ ኮድ «1» የለም ላሉ ኮድ «2» መሞላቱን ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 43:- <u>ባለፉት 7 ቀናት ሲሰሩበት የነበረው ሥራ ወይም ሲሰሩበት የነበረውን ድርጅት ለመቀየር ጥረት አድርገው ነበር?</u> :-ይህ ጥያቄ ወደዚህ ዓምድ የመጡ ግለሰቦችን ሁሉ ስለሚመለከት ለሁሉም ግለሰቦች መረጃ ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ያስፈልጋል:: አሁን የሚሰሩበትን ድርጅት/ሥራ ለመቀየር ጥረት አድርገው ከነበረ «አዎን» ተብሎ ኮድ «1» የለም ላሉ ደግሞ ኮድ «2» መሞላቱን ማጣራት ያሻል:: በተጨማሪም እዚህ ዓምድ ውስጥ የተጠየቁ ሰዎች «የስራ አጥነት» ጥያቄ ስለማይመለከታቸው ሁሉም ከዓምድ ዓምድ 44-46 ሳይጠየቁ በቀጥታ ወደ ዓምድ 47 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

*ዓምድ 44 - 46:- <u>ሥራ አጥነት (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)</u>*

ዓምድ 44:- <u>ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?</u> መጀመሪያ በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የሚሞላላቸው በክፍል 3 ዓምድ 28 ላይ የለም መልሰው ኮድ «4» ለተሞላላቸው ግለሰቦች መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል:: ለሌሎች ግለሰቦች ግን ካርድ ኮለሞቹ በሠረዝ «-»

ይታለፋሉ:: ነገር ግን ምንም እንኳን በዓምድ 28 ኮድ 4 ቢሞላላቸውም ይህንን ዓምድ ለመጠየቅ ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በታች ከሆነ እንደቀሩት ሁሉ ለነሱም በሰረዝ «-» መታለፉን ማስተዋል ያስፈልጋል::

ለዚህ ዓምድ የቀረቡት አማራጮች አዎን ብለው ለመለሱ ኮድ «1» እና የለም ላሉ ኮድ «2» ስለሆኑ በተገቢው ካርድ ኮለም ከሁለቱ ኮዶች አንደኛው ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል:: ከዚያም አዎን ብለው ኮድ «1» የተሞላላቸው ዓምድ 45ን ተሻግረው ወደ ዓምድ 46 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 45:- ለምንድነው ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት?:- በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 44 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ምንም ጥረት ላላደረጉ ግለሰቦች ብቻ ነው:: ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉበት ምክንያት በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት 11 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል:: የተሰጡት ኮዶች ከ01 - 11 ስለሆኑ በካርድ ኮለሞቹ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 46:- በሚቀጥለው አንድ ወር ሥራ ቢገኝልዎት ለመስራት ዝግጁ ነዎት?:- ለዚህ ጥያቄ አዎን ብለው የመለሱ ግለሰቦች ኮድ «1» የለም ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ «2» እንደተሞላላቸው በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ መታየት የሚገባቸው ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ክፍል 4 ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ

ዓምድ 47-51:- ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ

ዓምድ 47 :- ባለፉት 12 ወራት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሥራ ሰርተዋል?:- ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች «አዎን» እና «የለም» ሲሆኑ በዚሁ መሠረት በዓምዱ ሥር «አዎን» የሚለው ቃል ከተፃፈ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» መፃፉን ወይም ከላይ «የለም» ከተፃፈ ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ኮድ «2» መፃፉን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: ይህ ሁሉ ከተረጋገጠ በኋላ «የለም» ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዮቹን ዓምዶች ማለትም ከዓምድ 48-50 ሳይጠየቁ በሰረዝ «-» መታለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 48:- በሁሉም ምርታማ ሥራዎች ባለፉት 12 ወራት በጠቅላላው ለምን ያህል ወራት ነበር የተሰማሩት? ይህንን ጥያቄ የሚጠየቁት በዓምድ 47 «አዎን» ብለው ኮድ «1» የተሞላላቸው ስለሆኑ በ12ቱ ወራት በስራ የተሠማራባቸው ጊዜዎች ከተሠጡት 5 አማራጮች አይወጣም:: ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከጥያቄው ግርጌ ከተዘረዘሩት ከ1-5 ኮዶች ውጭ መሆን የለባቸውም::

ዓምድ 49:- ባለፉት 12 ወራት የተሰማሩበት የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድን ነው?:- ይህ ዓምድ የሚሞላው ልክ ዓምድ 29 በተሞላው አይነት ሲሆን አልፎ አልፎ ተመሳሳይነት ይኖረዋል:: ይህም ማለት ባለፉት 7 ቀናት የግለሰቡ ዋነኛ ሥራ ዓይነቱ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር ቢሆን በዚህም ዓምድ ተደግሞ ሊሞላ ይችላል:: ነገር ግን ያኟ ሰው ያለፉት 12 ወራት ዋነኛ የስራ ዓይነት ከባለፉት 7 ቀናት የተለየ ከሆነ የተለየ ኮድ ይሰጣቸዋል:: ቢሆንም ግን በዓምድ 29 ያለንን ዕንሰ-ሀሳብ እዚህም ላይ መጠቀም ስለሚገባን ዝርዝሩን ከዚሁ መመሪያ ዓምድ 29ን ማየት ያስፈልጋል:: በተጨማሪም እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጠየቁ ግለሰቦች ዕድሜአቸው 18 ዓመትና በላይ መሆኑን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው::

ዓምድ 50:- ዋነኛ ሥራዎን ያከናወኑበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው? በተመሣሣይ መልኩ ይህም ዓምድ እንደ ዓምድ 31 ግለሰቦች የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል:: ስለሆነም በዓምድ 31 የተጠቀምነው ቴክኒክ ከዚህ ዓምድ ጋር ተመሣሣይ ስለሆነ በዛው ዓይነት የተሞላውን የድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠውን አገልግሎት አይነት ከተዘጋጀው «የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ዝርዝር» መጽሀፍ በመውሰድ ይሞላል:: ለበለጠ ማብራሪያ በዚሁ መመሪያ ውስጥ ዓምድ 31ን ይመልከቱ:: ይህ ዓምድ የተሞላላቸው ግለሰቦች ቀጣይ ዓምድ ስለማይመለከታቸው ዓምድ 51ን ሳይጠየቁ በሰረዝ «-» ወደ ዓምድ 52 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያሻል::

ዓምድ 51:- ሥራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነበር?:- ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 47 ላይ ኮድ 2 ለተሞላላቸው ቢሆንም ዕድሜአቸው 18 ዓመትና በላይ መሆኑን በደንብ ማየት ተገቢ ነው:: በዚህ ዓምድ

የተሰጡት አማራጮች ከ0-8 ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ ከተሞላ መስተካከል ያሻዋል:: በመሆኑም ስራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት ለዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ፣ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 52:- <u>የልጅ/ጅቷ ዕድሜ ከ5-17 ነው?:-</u> ይህ ዓምድ ሁሉንም የቤተሰብ አባላት የሚመለከት ሲሆን ለቀጣይ ቅፆች ዋና መሠረት በመሆኑ ስህተት ካለ በትክክል መታረም አለበት:: በዚህ የማጣሪያ ጥያቄ በቤተሰቡ ውስጥ ምን ያህል ልጆች ለጥናቱ የተመረጡ መሆናቸውን የሚጣራበት ነው:: ስለሆነም ዕድሜአቸው ከ5-17 ለሆኑ ልጆች ኮድ «1» ተሞልቶ በስተቀኝ ያለው ቁጥር መከበቡን እና ዕድሜአቸው ከ5-17 ውስጥ ላልሆኑ የቤተሰብ አባላት ደግሞ ኮድ «2» ተሞልቶ ደግሞ በስተቀኝ ያለው ቁጥር ያለመከበቡም ማረጋገጥ ወሳኝ ነው:: ይህንንም በዓምድ 16 የተሞላውን ዕድሜ በማየት ችግሩን ወዲያው ማወቅ ያስፈልጋል::

# ምዕራፍ IV

## ቅፅ 1 ክፍል 5- ስለቤተሰቡ እና ቤተሰቡ ስለሚኖርበት ቤት መረጃ መጠይቅን ማረም

<u>ከዓምድ 53-58</u> <u>የቤተሰብ ፍልሰት ሁኔታ</u>

<u>ዓምድ 53:-</u> <u>ይህ ቤተሰብ ከተመሠረተ ጀምሮ ከዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ውጪ ሌላ ቦታ በመደበኛነት ኖሮ ያውቃል?:-</u> ይህ ዓምድ የተመረጠው የቤተሰብ አሁን በሚገኝበት ወረዳ ገጠር/ከተማ ውጪ ሌላ ቦታ በመደበኛነት ኖሮ እንደሆነ የሚጠይቅበት ነው:: ለዚህም የተለያዩ አማራጮች ኮድ 1 እና 2 ከጥያቄው ሥር ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ ውስጥ በሚገኘው ንዑስ ዓምድ የሚሞላው ቁጥር ከ1 ወይም 2 ካሉት ቁጥር ውጭ መሆን የለበትም:: ኮድ 2 ለተሞላላቸው ከዓምድ 54-58 ምንም ሳይሞላ በሰረዝ መታለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ነገር ግን ኮድ 1 ለተሞላላቸው ከዓምድ 54-58 ያሉትን ተሞልቶ ከተገኘ ተመልሶ ዓምድ 53ን ኮድ 1 እነደተሞላ ማድረግ ይገባል::

*<u>ዓምድ 54-58</u>- <u>ለፈለሱ ቤተሰቦች (በዓምድ 53 ኮድ 1-4 ለተሞላላቸው)</u>*

<u>ዓምድ 54:-</u> <u>ቤተሰቡ ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የትኛው ክልል ይኖር ነበረ?:-</u>በዓምድ 53 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ቤተሰቦች ቀደም ሲል ይኖሩ የነበሩት የትኛው ክልል እንደነበረ ተጠይቀው የተሞላው ክልል ስም ተመጣጣኙ ኮድ በዓምዱ ሥር በሚገኙት ካርድ ኮለሞች ላይ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የኮዶቹም ዝርዝር ከታች ቀርቧል:: የክልል ኮድ ሳይሞላ ከመጣ ከዓምድ 56 ከተሞላው የከተማ ስም በመነሳት መሙላት ይቻል ይሆናል::

<u>የክልሎች ዝርዝርና ኮድ</u>

| | |
|---|---|
| 01= ትግራይ ክልል | 07= ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል |
| 02= አፋር ክልል | 12= ጋምቤላ ክልል |
| 03= አማራ ክልል | 13= ሐረሪ ክልል |
| 04= ኦሮሚያ ክልል | 14= አዲስ አበባ |
| 05= ሶማሌ ክልል | 15= ድሬዳዋ |
| 06= ቤንሻንጉል- ጉምዝ ክልል | 16= ከኢትዮጵያ ውጭ (የአገሩ ስም ይሞላል) |

<u>ዓምድ 55:-</u> <u>ቤተሰቡ ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የየትኛው ዞን ይኖር ነበረ?:-</u>በዓምድ 55 ካርድ ኮለሞች የተገለፀው የዞን ኮድ በዓምድ 54 የተመለከተው ክልል ሥር የሚገኝ መሆኑ መረጋገጥና ለዞኑ የተሰጠውም ኮድ ትክክል መሆኑ ይጣራ:: ለዚህም እንዲረዳ በዚህ መመሪያ ዕዝል 2 የተሰጡትን የኮድ ዝርዝሮች ይመልከቱ:: በዚህ ዓምድ የተሰጠው ካርድ ኮለም 3 ሲሆን የሚሞላው ግን ባለ ሁለት ዲጂት የዞን ኮድ ስለሆነ አንዱ ካርድ ኮለም በመረጃ ሠብሳቢዎች መዘጋቱን ማረጋገጥና አስተካክሎ መፃፍ::

ዓምድ 56:- ቤተሰቡ ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ይኖርበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ነበር ወይስ ገጠር?:- በዚህ ዓምድ ሥር የሚሰፍረው የከተማ ስም ወይም «ገጠር» የሚለው ቃል ነው:: በካርድ ኮለሙም ውስጥ ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ ነው መገኘት ያለበት:: ነገር ግን ከላይ ከተገለጸው ውጭ ለከተማ የከተማው ስም መጻፍ ሲኖርበት «ከተማ» ተብሎ ከመጣ ስህተት ሊሆን ስለሚችል ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ ይገባል:: በተጨማሪም ለከተማ ኮድ 1 ለገጠር ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በዞኖች ሥር የሚገኙ ከተሞች ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ዕዝል ያቀረበ ስለሆነ በዓምዱ የተፃፈው የከተማ ስም ዝርዝር መሠረት ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል::

ዓምድ 57: ቤተሰቡ አሁን ወደሚኖርበት ቦታ ለመምጣት/ለመቀየር ያበቃው ዋነኛ ምክንያት ምንድ ነው?:-ይህ ዓምድ በዓምድ 53 ላይ ፈልሰው ማለትም ኮድ 1 ለተሞላላቸው ቤተሰቦች በምን ምክንያት እንደፈለሱ/የቀድሞ መኖሪያቸውን እንደለቀቁ/ ተጠይቆ የሚሰጡ ምክንያቶች ከተዘረዘሩት አማራጮች ተስማሚው ኮድ የተሞላበት ዓምድ ነው:: በካርድ ኮለሙም የሚሞሉት ቁጥሮች ከ1-8 ያሉት ብቻ መሆን አለባቸው:: በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሙ ኮድ 8 ተሞልቶ የሰጡት ምክንያት በዓምዱ ከተመዘገበ ይህን ምክንያት በትኩረት በመመርመር ከጥያቄው ሥር ከ1-7 ከተዘረዘሩት መልሶች ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ከካርድ ኮለሙ ኮድ 8ን በመሰረዝ ተቀራራቢውን ኮድ መሙላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 58 :-ቤተሰቡ አሁን በሚኖርበት የመኖሪያቦታ ያለማቋረጥ ለምን ያህል ዓመት ቆይቶአል?:-ይህ ዓምድ የተመረጠው የቤተሰብ አሁን በሚገኝበት ወረዳ ገጠር/ከተማ ውስጥ ያለማቋረጥ ለስንት ዓመት ኖሮ እንደሆነ የሚጠይቅበት ነው:: ለዚህም የተለያዩ አማራጮችኮድ 0-7 ከጥያቄው ሥር ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ ውስጥ በሚገኘው ንዑስ ዓምድ የሚሞላው ቁጥር ከ0-7 ካሉት ቁጥር ውጭ መሆን የለበትም::

ዓምድ 59:- የቤቱ ይዞታ ምንድነው?:-ቤተሰቡ የሚኖርበት ቤት ይዞታ አይነት የሚጠየቅበት ሲሆን አማራጮቹ ከኮድ 1-6 ተዘርዝረዋል:: ካርድ ካለሙ በዚህ መሰረት መሞላቱንና ከኮድ 1-4 ስለተሞላላቸው ወደ ዓምድ 61 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ::

ዓምድ 60:- ቤተሰቡ በወር የሚከፈለው የኪራይ መጠን ስንት ነው?:-በዓምድ 59 ኮድ 5 ወይም 6 ለተሞላላቸው ብቻ የሚከፍሉት የቤት ኪራይ መጠን የተሞላ መሆኑን ማረጋገጥ:: ከኮድ 1-4 ለተሞላላቸው ደግሞ ወደ ዓምድ 61 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ:: እንዲሁም የኪራይ መጠን ሲሞላ ሳንቲሞች ወደ ሙሉ ብር ተጠጋግቶ ስለሆነ በዓምዱ የተሞላውን የብር መጠን መሰረት አድርጎ በንዑስ ዓምዶች በትክክለኛው አሞላል እንዲስተካከል ማድረግ ተገቢ ነው::

ዓምድ 61:- የቤቱ ግድግዳ አብዛኛውን የተሰራው ከምንድን ነው?:-ቤተሰቡ የሚኖርበትን ቤት ግድግዳ በአብዛኛው የተሰራው ከምን እንደሆነ የሚጠየቀበት ሰለሆነ ከተዘረዘሩት አማራጮች ከኮድ 1-8 በንዑስ ዓምድ ይሞላል:: ኮድ 8 ለተሞላላቸው ከዝርዝሩ በመነሣት ከኮድ 1-7 ከተዘረዘሩት አማራጮች ሊካተቱ የሚችሉትን ማስተካከል ያስፈልጋል::

ዓምድ 62:- የቤቱ ጣሪያ አብዛኛው የተሰራው ከምንድን ነው?:-የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው ከምን እንደተሰራ የሚጠየቅበት ሲሆን ከኮድ 1-6 ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ በንዑስ ዓምዱ መሞላት ይኖርበታል:: መረጃ ሰብሳቢዎች በዚህ አምድ የፃፉት ማስታወሻ መኖሩን በማጣራት ከተቆጣጣሪው ጋር በመነጋገር አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ያስፈልጋል::

ዓምድ 63:- የመኖሪያ ቤቱ ስንት ክፍሎች አሉት?:-ቤቱ ስንት ክፍሎች እንዳሉት በዚህ ዓምድ ሲጠየቅ በንዑስ ዓምዱ የሚሞላው ግን የክፍሎቹ ብዛት ሳይሆን በተዘረዘረው አማራጭ መልሶች መሠረት ነው:: በዚህም መሠረት ቤቱ 4 እና ከዚያ በላይ ክፍሎች ካሉት ኮድ 4 ብቻ የሚሞላ ስለሆነ በዚህ መሠረት ንዑስ ዓምዱ መሞላቱን ማረጋገጥ::

ዓምድ 64:- የመኖሪያ ቤቱ ምን ዓይነት መፀዳጃ አለው?:-መኖሪያ ቤቱ ምን ዓይነት መፀዳጃ እንዳለው የሚጠየቅበት ዓምድ ነው:: በዚህ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢዎች የገለፁት ማስታወሻ ከተገኘ ከዚያ በመነሳት የተሞላውን መልስ ላይ አስፈላጊውን እርማት ማድረግ:: ለምሣሌ በማስታወሻ ላይ በአንድ የመፀዳጃ ቤት ጉድጓድ የተለያዩ መውጫና

መግቢያ በር በመስራት የተለያዩ ቤተሰቦች ይጠቀሙበታል ተብሎ ቢገለፅ በንዑስ ዓምዱ መሞላት ያለበት ኮድ 4 ነው::

ዓምድ 65:- <u>መኖሪያ ቤቱ ምን ዓይነት ማድቤት አለው?</u>:-በዚህ ዓምድ የቤቱ የማድቤት ሁኔታ የሚጠየቅበት ሲሆን ከተሰጡት ከኮድ 1-5 አማራጮች ውስጥ በንዑስ ዓምድ መሞላቱን ማረጋገጥ::

ዓምድ 66:- <u>የቤቱ ነዋሪዎች የመጠጥ ውሃ በአብዛኛው የሚያገኙት ከየት ነው?</u>:-ቤተሰቡ በአብዛኛው የመጠጥ ውሃ ከየት እንደሚያገኝ የሚጠየቅበት ሲሆን ከኮድ 1-7 ዓማራጭ መልሶች ተዘርዝረዋል:: ከእነዚህ ውጪ መረጃ ሰብሳቢዎች በማስታወሻ ዘርዝረው ከሆነ በአብዛኛው የሚለውን ከግንዛቤ በማስገባትና ከአካባቢው ሁኔታ በመነሣት ወደተስማሚው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ተገቢ ነው:: እንዲሁም በኮድ 4 የተሰጠው አማራጭ ቤተሰቡ የመጠጥ ውሃ ከግቢ ውጪ በግዥ የሚያገኝ ከሆኑ ሲሆን ከግቢ ውስጥ በግዥ ከሆነም ኮድ 4 መሞላት አለበት::

ዓምድ 67:- <u>የቤቱ ነዋሪዎች ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ ምን ዓይነት ማገዶ ይጠቀማሉ?</u>:-ቤተሰቡ በአብዛኛው የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት ከኮድ 1-6 የተዘረዘሩት ውስጥ በንዑስ ዓምድ መሞላት አለበት:: ከዚህ ወጪ ከተዘረዘሩት የማገዶ ዓይነቶች በጣምራ እንደሚጠቀሙ ከተገለፀ ወደአስፈላጊው ኮድ (ከኮድ 1-5) እንዲካተት መደረግ አለበት::

ዓምድ 68:- <u>ቤተሰቡ የሚከተሉት ቋሚ ንበረቶች አሉት?</u>:-ቤተሰቡ ከፊደል A-O የተዘረዘሩት ቋሚ ንበረቶች ያሉት መሆኑን የሚጠየቅበት ስለሆነ ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት ዓይነት እንደአስፈላጊነቱ አዎን (ኮድ 1) ወይም የለም (ኮድ 2) መክበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የተዘለሉ ከአጋጠመ ከተቆጣጣሪው ጋር በመነጋገር አስፈላጊው ኮድ እንዲከበብ ማድረግ ይገባል:: በተጨማሪም በዓምድ 59 የቤተሰቡ መኖሪያ ዓይነት የግል (ኮድ 1) የተከበበ ከሆነ በዚህ ዓምድ ቤት አለው የሚለው መከበቡን ማመሳከር ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 69 - 70B</u>:-የቤተሰቡ ግምታዊ የወር ወጪ በዓምድ 69 እንዲሁም የወር ግምታዊ ገቢ በከተማ በዓምድ 70A እና የዓመታዊ ገቢ በገጠር በዓምድ 70B የሚጠየቅበት ነው:: ይህን በተመለከተ ከመረጃ ሰብሳቢዎች የሚሰጡ ማስታወሻዎችና የሂሳብ ስሌቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ከማስታወሻዎች በመነሣት አስፈላጊውን የመልስ እርማት ማድረግ ያስፈልጋል::

## ምዕራፍ V

## የቅጽ 2-ዕድሜያቸው ከ5-17 ዓመት ስለሆኑ ልጆች የሥራ ስምሪት ሁኔታ መጠይቅን ማረም

በዚህ ቅጽ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚመለከቱት ዕድሜያቸው ከ5-17 ዓመት ለሆኑ ልጆች ስለሆነ ከቅጽ-1 ዓምድ 52ን በመመልከት በትክክል ከዓምድ 16 እድሜአቸው ከ5-17 መሆኑ ተረጋግጦ ኮድ 1 በካርድ ኮለሙ የተሞላላቸውና እና በስተቀኝ በኩል የተሞላው የመስመር ቁጥራቸው መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በተጨማሪ ዓምድ 52 ላይ ኮድ 2 የተሞላላቸው ሰዎች ወደዚህ ክፍል መምጣት ስሌላባቸው አለመምጣታቸውም ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

### <u>ክፍል-1 የአካባቢ መለያ</u>

ምድ 1-10 የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ ከዓምድ 1 እስከ 10 ከቅጽ 1 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ምድ 11 የልጅቷ ስም ከቅጽ 1 ዓምድ 13፤ መወራረሱን ማረጋገጥ

ምድ 12 የልጅቷ የመስመር ቁጥር ከቅጽ 1 ከዓምድ 12 ማረጋገጥ

ዓምድ 13 መጠይቁ ቤተሰቡ ውስጥ ካሉት ልጆች መካከል ስንት ስንተኛ ነው?
ለሚለው ጥያቄ ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ለሁለተኛው ካርድ ኮለም የሚሞላው ቁጥር ቤተሰቡ ውስጥ ጥናቱ የሚመለከታቸው ዕድሜአቸው ከ5-17 የሆናቸውን ልጆች ብዛት ወይም በቅጽ-1 አምድ 52 ኮድ 1 ተሞልቶላቸው በቀኝ በኩል የተሞላው የመስመር ቁጥራቸው የተከበበላቸው ልጆች ብዛት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለመጀመሪያው ካርድ ኮለም ግን ለመጀመሪያው ልጅ ፲ ለሁለተኛው ፳ ለሶስተኛው 3... ወዘተ. እየተባለ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ቤተሰቡ ውስጥ ጥናቱ የሚመለከታቸው ልጆች 3 ቢሆኑ ለመጀመሪያው ልጅ 1 ከ ፫ ለሁለተኛው 2 ከ3 እና ለሦስተኛው 3 ከ3 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ክፍል 6 የፍልሰት ሁኔታ

601 ከተወለደች ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቤተሰብ ጋር ያለማቋረጥ በመደበኝነት አብሮ/ራ ኖሯል/ኖራለች ? በዚህ ጥያቄ ልጆች ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ አሁን ከሚኖሩበት ቤተሰብ ጋር በመደበኝነት ያለማቋረጥ ኖረው ከሆነ ኮድ 1 ኖረው ካልሆነ ደግሞ ኮድ 2 ተከቦ መጥቷል:: ስለዚህ ኮድ 1 የተከበበላቸው ልጆች ተከታዮቹን ጥያቄዎች ሳይጠየቁ ወደ ጥያቄ 701 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ነገር ግን ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣይ ጥያቄዎችን ማለትም እስከ 605 ያሉትን መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው።።

602 ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ቦታ የት ነው?:-ይህ ጥያቄ የሚጠየቅላቸው ልጆች በጥያቄ 601 ኮድ 2 የተከበበላቸው ማለትም ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ በመደበኛነት ከቤተሰቡ ጋር ያለማቋረጥ ያልኖሩ ልጆች ናቸው:: ስለዚህ ለክልልና ለዞን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የክልሉና የዞኑ ስም መሞላቱንና ለክልልና ለዞን በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ላይ ለክልሉና ለዞኑ የተሰጡት ኮዶች በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ልጆች ለመጨረሻ ጊዜ ይኖሩበት የነበረው ከአገር ውጪ ከሆነ ለክልል በተሰጠው ቦታ ውጪ አገር ተብሎ ተሞልቶ ለወጪ አገር የተሰጠው ኮድ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ነው:: ለዚህም እንዲረዳ በዚህ መመሪያ ዓምድ 55 የተሰጠውን ማብራሪያ እና ዕዝል 2 የተሰጡትን የኮድ ዝርዝሮች ይመልከቱ::

603. ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ቦታ ከተማ ነው ወይስ ገጠር? :-ልጅ/ቷ ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ቦታ ከተማ ከሆነ ኮድ 1 ተከቦ መጥቷል:: ኮድ 1 ከተከበበ የከተማው ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ነገር ግን ገጠር ከሆነ ኮድ 2 ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

604. ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ በኖረበት/ችበት ስፍራ ምን ያደርግ/ታደርግ ነበር? :-ለዚህ ጥያቄ አመራጭ መልስ ይሆናሉ ተብሎ 4 አመራጮች ተሰጥተዋል:: ከነዚህ ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ልጆች ለመጨረሻ ጊዜ ይኖሩበት የነበረው ስፍራ ያደርጋሉ/ይሰራሉ ተብሎ የሚገመቱትን ምክንያቶች ከኮድ/ 1 እስከ 3 ተዘርዝረዋል:: በተጨማሪ ከነዚህ ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ደግሞ በሌላ ተገልጾ ኮድ 4 ተከቦ መጥቷል:: ነገር ገን በሌላ የተገለፀው ከኮድ 1 እስከ 3 ባሉት አማራጮች ውስጥ የሚካተት ከሆነ ማስተካከል ያስፈልጋል::

605. ከዚህ ቤተሰብ ጋር ለመኖር ያመጣው/ጣት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው ? :-ልጆች አሁን ከሚኖሩበት ቤተሰብ ጋር ለመኖር ያመጣቸዋል ተብለው የሚገመቱ 8 ምክንያቶች በአመራጭነት ቀርበዋል:: ከነዚህ ውጪ ከሆነ ደግሞ በሌላ ተገልጾ ኮድ 9 እንዲከበብ ተደርጓል:: ስለዚህ ከነዚህ 9 አማራጮች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በተጨማሪ በሌላ የተገለጸው ከ1-8 ከተሰጡት አመራጮች ጋር ተቀራራቢ ከሆነና የሚካተት ከሆነ ለተቆጣጣሪው በማሳየት ማስተካከል ያስፈልጋል::

606. አሁን በሚኖሩበት/በምትኖርበት የመኖሪያ ቦታ ለምን ያህል አመት ቆይቷል/ታለች ?:-ይህ ጥያቄ አሁን እየኖሩበት ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ ለምን ያህል ዓመት እንደቆዩ የሚጠየቅበት ነው:: ስለዚህ ከተሰጡት ስምንት አማራጮች ውስጥ አንድ ኮድ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ በቂ ነው::

## ክፍል 7: የትምህርት ሁኔታ

701. በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት እየተከታተልክ/ሽ ነው? ምን አይነት ትምህርት ?:-በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት እየተከታተሉ ላሉ ልጆች ኮድ ፲ የሙያ/የቴክኒክ ሥልጠና እየተከታሉ ላሉ ልጆች ኮድ ፳ መደበኛ

ያልሆነ ትምህርት እየተከታተሉ ላሉ ልጆች ደግሞ ኮድ 3 እና መደበኛም ሆነ መደበኛ ያልሆነ ለማይከታተሉ ልጆች ኮድ 4 ተሞልቶ መጥቷል:: ስለሆነም ኮድ 1 የተሞላላቸው ልጆች ወደ ሚቀጥለው ጥያቄ ማለትም 702 ማለፋቸውን፣ ኮድ 2 የተሞላላቸው ድግሞ ወደ ጥያቄ 703 ማለፋቸውን እና ኮድ 3 እና 4 የተሞላላቸው ልጆች ደግሞ ወደ ጥያቄ 704 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

702. <u>አሁን የምትከታተለው/የሚትካታታይው የክፍል ወይም የትምህርት ደረጃ ስንተኛ ነው?</u>:-በመጀመሪያ ይህ ጥያቄ የሚሞላላቸው ልጆች ከላይ ለጥያቄ 701 ኮድ 1 የተሞላላቸው ማለትም በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት እየተከታተሉ ያሉ ልጆች ብቻ ናቸው:: ለዚህ ጥያቄ የክፍሉን ደረጃ ለመሙላት ሁለት ካርድ ኮለም የተሰጠ ሲሆን በነዚህ ካርድ ኮለሞች ውስጥ የሚሞላው ቁጥር ከ1-13 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ቅጽ 1 ዓምድ 20 ላይ የጨረሱት ክፍል ስንተኛ ነው ለሚለው ጥያቄ ጋር ማመሳከር ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ጥያቄ 702 ላይ 8ኛ ክፍል የተሞላላቸው ልጆች ዓምድ 20 ላይ የተሞላላቸው 7ኛ/ሰባተኛ/ ክፍል ሊሆን ይችላል፡፡

703. <u>ባለፈው ሳምንት መደበኛ ትምህርት ወይም ስልጠና ተከታትሎ/ላ ነበር?</u>:-ይህንን ጥያቄ የሚጠየቁት ልጆች ለጥያቄ 701 ኮድ 1 እና 2 የተከበበላቸው ነው:: ለዚህ ጥያቄ ከተሰጡት 4 አማራጭ መካከል ከኮድ 1 እስከ 3 የተከበበላቸው ልጆች ወደ ጥያቄ 801 ማለፋቸውንና ቀጣይ ጥያቄዎችን አለመጠየቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ኮድ 4 የተከበበላቸው ልጆች ደግሞ ቀጣይ ጥያቄዎችን ማለትም 704 እና 705ን ሳይዘለሉ መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

704. <u>ከዚህ ቀደም መደበኛ ትምህርት ተከታትሎ/ላ ነበር ?</u>:-ይህንን ጥያቄ የሚጠየቁ ልጆች ከላይ ለጥያቄ 703 ኮድ 4 የተሞላላቸው ልጆችና ጥያቄ 701 ላይ በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ለሚከታተሉ ማለትም ኮድ 3 የተሞላላቸውና ምንም አይነት ትምህርት ለማይከታተሉ ልጆች ማለትም ኮድ 4 የተሞላላቸውን ነው:: ለዚህ ጥያቄ 4 አመራጮች የተሰጡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

705. <u>መደበኛ ትምህርት/ስልጠና ያልተከታተለበት/ችበት ዋናው ምክንያት ምንድን ነው:</u>-ይህንን ጥያቄ የሚጠየቁ ልጆች በጥያቄ 701 መደበኛ ያለሆነ ትምህርት እከታተላለሁ ብለው ኮድ 3 ፣ መደበኛም ሆነ መደበኛ ያልሆነ አልከታተለም ብለው ኮድ 4 የተሞላላቸው እና በጥያቄ 703 ላይ ባለፈው ሳምንት ትምህርት እንደማይከታተሉ ተረጋግጦ ኮድ 4 የተሞላላቸውን የሚመለከት ሲሆን ልጆች ትምህርት ላይከታተሉ ይችላሉ ተብሎ የሚጠበቁትን ምክንያቶች ከኮድ 01-14 ተገልጿል:: በተጨማሪ ከነዚህ ውጪ ከሆነ ደግሞ በሌላ ተገልጾ ኮድ 15 እንዲከበብ ተደርጓል:: ስለዚህ ከነዚህ ኮዶች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::

## <u>ክፍል 8:- ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ሁኔታና ምንም አለመስራት</u>

<u>801:- ስም በቤት ውስጥ ወይም ለቤተሰብ ግልጋሎት በመስጠት በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳጊዎቻቸው ቤት ውስጥ ያለክፍያ በመደበኛነት ይሰራሉ?</u>:-ይህ ጥያቄ ለሁሉም ቅጹ ለሚመለከታቸው ልጆች የሚጠይቅ ሲሆን አማራጮቹም:አዎን በየቀኑ-ኮድ 1፣ አዎን ቅዳሜና እሁድ -ኮድ 2፣ አዎን አልፎ -ኮድ 3፣ የለም ምንም የቤት ውስጥ ስራ አይሰራም -ኮድ 4 ናቸው፡፡

አዎን አልፎ አልፎ ብለው ኮድ 3 የተሞላላቸው ወደ ጥያቄ 803 እንዲሁም ምንም አይሰሩም ተብሎ ኮድ 4 የተሞላላቸው ወደ 804 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ሲያስፈልግ ኮድ 1 እና ኮድ 2 የተሞላላቸው በሙሉ ቀጣዩን ጥያቄ 802 መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

802:-<u>በቀን በአማካኝ ለስንት ሰዓት ይሰራል/ትስራለች?</u>:-ይህ ጥያቄ በጥያቄ 801 ላይ ኮድ 1 እና ኮድ 2 የተሞላላቸው ብቻ መጠይቁን ማረጋገጥ እንዲሁም ከተሰጡት አማራጮች መካከል የአንዱን ኮድ ብቻ መከበቡን ማየት ያስፈልጋል::

ከፊደል A እስከ J ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ቢያንስ ለአንዱ እንኳን አዎን የሚል መልስ ከተመለሰ ለI የግድ ኮድ 2 መሞላት ያለበት ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ከA-J ላሉት በሙሉ ምንም አልሰራም ተብሎ ኮድ 2 ከተሞላ ለI የግድ ኮድ 1 መሞላት እንዳለበት አውቀን በዚሁ መሠረት መሰራቱን ማየት አለብን::

<u>803:-ባለፉት 7 ቀናት ልጁ/ልጅቷ የሠራውን/የሠራችውን የቤት ውስጥ ግልጋሎቶች ይግለፁልኝ?</u>

ይህ ጥያቄ በጥያቄ 801 ከኮድ 1-3 ለተከበበላቸው ብቻ የሚጠየቅ ስለሆነ በዚሁ መሠረት መጠየቁን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከፊደል A እስከ J የተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ያጋጥማሉ ተብለው የተቀመጡ የቤት ውስጥ

ሥራዎች ስለሆኑ ለያንዳንዳቸው መሠራት አለመሠራቱ ተጠይቆ አዎን ወይም የለም በሚሉት አማራጭ መልሶች ስር ካሉት ኮዶች አንዱ ብቻ የግድ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ከፊደል A እስከ J የተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ቢያንስ አንዱ እንኳን አዎን የሚል መልስ ከተመለሰ ለፊደል L የግድ ኮድ 2 መሞላት ያለበት ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ከፊደል A እስከ J ላሉት በሙሉ ምንም አልሠራም ተብሎ ኮድ 2 ከተሞላ ለፊደል L የግድ ኮድ 1 መሞላት እንዳለበት አውቀን በዚሁ መሠረት መሠራቱን ማየት አለብን::

804:-ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ሥራ ሰርቷል?:-ይህ ጥያቄ የማጣሪያ ጥያቄ ሲሆን ልጆች ምርታማ ሥራ መስራታቸውን የምናጣረበት ነው ። ለዚህ ጥያቄ አዎን የሚል መልስ ከተሞላ በቅጽ -1 ዓምድ 27 ኮድ 1 መሞላቱን ወይንም በዓምድ 28 ከ ኮድ 1-3 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁምለዚህ ጥያቄ የለም ተብሎ ኮድ 2 ከተሞላ በቅጽ -1 ዓምድ 28 ኮድ 4 መሞላቱን ማየት ያስፈልጋል::

805:- ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ያልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ ሠርቷል/ሠርታለች?:-ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ ልጆች ያለውን ሳምንት በትምህርት ወይንም በቤት ውስጥ ሥራ ማሳለፋቸውን ለማወቅ ሲሆን የሚጠየቀውም በጥያቄ 804 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ብቻ ስለሆነ በዚሁ መሠረት መጠየቁን ማየት ይገባል:: የጥያቄው አማራጭ መልሶችም አዎን ኮድ 1 እና የለም ኮድ 2 ስለሆኑ ከሁለት አንዱ መከበቡን ማየት ያስፈልጋል:: እንዲሁም አዎን ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ሁሉ ወደ ጥያቄ 901ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

806:- ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ትምህርት ያልተከታተለችበት ወይንም ምንም አይነት ሥራ ያልሰራችበት ምክንያት ምን ነበር?:- ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 804 እና 805 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ብቻ ሲሆን ከኮድ 1-6 ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማየት ይገባል::

## ክፍል -9 ባለፉት በማናቸውም ጊዜያት በሥራ ላይ ተሰማርተው የማያውቁ ልጆች ከሠሩት ወይንም ከሚሠሩት ሥራ ጋር በተያያዘ የጤና እና የደህንነት ሁኔታን የተመለከቱ ጥያቄዎች::

901:-በማንኛውም ጊዜ (በሥራ ቦታ) በሥራ ላይ የደረሰበት/ባት ጉዳት ወይም ደግሞ በስራ ምክንያት ህመም ወይም ጉዳት ደርሶበት/ባት ያውቃሉ?:-ይህ ጥያቄ ለሁሉም ልጆች የሚጠየቅ ሲሆን አማራጭ መልሶቹም አዎን ኮድ 1፣ የለም ኮድ 2 እና ምንም ሰርቶ አያውቅም/አታውቅም ኮድ 3 ናው:: ስለዚህ ከተሰጡት 3 አማራጮች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማየት ሲገባ ኮድ 2 የተሞላላቸው ወደ ጥያቄ 911 እንዲሁም ኮድ 3 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ ጥያቄ 1105 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

902:-ልጁ/ጅቷ ህመም ወይም ጉዳት የደረሰባቸው ምን ያህል ጊዜ ነው?:- ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 901 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ብቻ ሲሆን ከቀረቡት አማራጭ መልሶች አንዱ ብቻ መከበቡን ማየት ይገባል::

903:-ልጁ/ልጅቷ ከደረሱበት/ባት ህመሞች ወይም ጉዳቶች ውስጥ ከበድ ያለው ህመም ወይም ጉዳት በደረሰበት/ባት ጊዜ የሚሰራበት/የምትሰራበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድን ነው?:-ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 901 አዎን ተብሎ ኮድ 1 ለተከበበላቸው ስለሆነ ይህንን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ለጥያቄው መልስ ነው ተብሎ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ የተገለፀውን በሚገባ በማጤንና ከኢንዱስትሪ ምደባና ኮድ ዝርዝር ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለሙ ውስጥ እንድንሞላ ይጠበቃል::

904:- ልጁ/ልጅቷ ከደረሱበት/ባት ህመሞች ወይም ጉዳቶች ውስጥ ከበድ ያለው ህመም ወይም ጉዳት የደረሰበት/ባት ምን ዓይነት ሥራ በሚሠራበት/በምትሰራበት ወቅት ነው/ነበር?:-ለዚህ ጥያቄም መልስ የሚጠበቀው በጥያቄ 901 አዎን ተብሎ ኮድ 1 ከተሞላ ብቻ ስለሆነ ይህንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንደዚሁም በጥያቄ 904 ለቀረበው ጥያቄ መልስ ነው ተብሎ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ የተገለፀውን በሚገባ በማጤንና ከሥራ ዓይነት ምደባና ኮድ ዝርዝር ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ኮድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ውስጥ እንድንሞላ ይጠበቃል::

905:- ልጁ/ልጅቷ ህመም ወይም ጉዳት የደረሰበት/ባት ከሆነ የህመሙ ወይም የጉዳቱ ዓይነት ምንድን ነው? (እስከ ሦስት ህመም ወይም ጉዳት ይዘርዝር):-በዚህ ጥያቄ በሚሠሩት ሥራ ምክንያት ህመም ወይም ጉዳት ደርሶብናል ያሉ ልጆች ከደረሱባቸው ህመሞች/ጉዳቶች መካከል ከፍተኛ የሆኑ እስከ 3 የሚደርሱ የህመም ወይም የጉዳት ዓይነቶች የተዘረዘሩ ሲሆን ለእነዚህ በቅደም ተከተል ለተዘረዘሩ የህመም ወይም የጉዳት ዓይነቶች ታች ከተዘረዘሩት ኮዶች ጋር በማገናዘብ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ተገቢ ኮዶችን እንድንሞላ ይጠበቃል::

906:-የደረሰበት ህመም ወይም ጉዳት ሥራ ለመስራት እንዳይችል/ትችል ከልክሎታል/ኗታል?:- ይህ ጥያቄ በጥያቄ 901 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ብቻ የሚጠየቅ ሲሆን ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማየት ያስፈልጋል::

907:-ስም ላይ ከደረሱ ህመሞች ወይም ጉዳቶች መካከል ከፍተኛ ለሆነው ምን አይነት ህክምና ተደርጎለታ/ተደርጎላታል?:- ለዚህ ጥያቄ 5 አማራጭ መልሶች የቀረቡ ሲሆን ኮድ 1 ከተሞላ ወደ 910፣ ኮድ 2 ከተበበ ወደ 909 እንዲሁም ኮድ 4 ወይም 5 ከተበበ ወደ 911 ማለፉን ማየት ይገባል::

908:-(ስም) በህክምና ተቋም ተኝተህ/ሽ የታከምክባቸው/ሽባቸው ቀናት ብዛት ምን ያህል ነበር?:- ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በ907 ኮድ 3 ለተሞላላቸው ብቻ ሲሆን ከ96 ቀናት በላይ ለተኙ ሁሉ 97 መሞላቱን ማየት ያስፈልጋል::

909:-(ስም) በጤና ባለሙያ የታከመው/የታከመችው የት ነበር?:- በጥያቄ 907 ኮድ 2 ወይም 3 ለተሞላላቸው ብቻ ሲሆን ለእያንዳንዱ አማራጭ አዎን ወይም የለም ከሚሉት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ መከበቡን ማየት ያስፈልጋል::

910:-(ስም) ለህክምና የወጣውን ወጪ ማን ከፈለ?:-በጥያቄ 907 ላይ ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ብቻ የሚጠይቅ ሲሆን ከፊደል A እስከ ፊደል D ድረስ ለተዘረዘሩት አማራጮች ለየአንዳንዳቸው ተጠይቆ አዎን ወይም የለም ከሚሉት መልሶች ውስጥ አንዱ መከበቡን ማየት ያስፈልጋል::

911:-መረጃ ሰብሳቢ:- ጥያቄ 804ትን ተመልከት/ች
(ስም) ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ሥራ ሰርቷል/ታለች?:- በጥያቄ 901 ላይ ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ለተሞላላቸው ብቻ የሚጠየቅ ሲሆን አማራጭ መልሶችም አዎን ሰርቷል/ታለች ኮድ 1 እና የለም አልሠራም/ራችምኮድ 2 ናቸው:: ለዚህ ጥያቄ ኮድ 1 ከተከበበ በጥያቄ 804 ላይ ኮድ 2 መከበቡን ማየት ያስፈልጋል:: እንዲሁም ኮድ 2 የተሞላላቸው ሁሉ ወደ 1105 ማለፋቸውን ማየት ይገባል::

912:-(ስም) በሥራ ላይ እያለ ወይም እያለች የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ይቀጠማል/ትጠቀማለች?:-በጥያቄ 911 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ብቻ የሚጠየቅ ሲሆን ከፊደል A እስከ ፊደል G ለተቀመጡት የአደጋ መከላከያ አይነት ለያንዳንዱ ተጠይቆ አዎን ወይም የለም ለሚሉት አማራጭ መልሶች ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 መከበባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል : በተጨማሪም ከA እስከ F ላሉት ለአንዳቸው እንኳን ኮድ 1 ከተሞላ ለGኮድ 2 መሞላት እንዳለበት በአንፃሩ ደግሞ ከA እስከ F ላሉት በሙሉ ኮድ 2 ከተሞላ ለG ኮድ 1 መሞላት እንዳለበት ማወቅ ይገባል::

913:-(ስም) የሚሠራውን/የምትሠራውን የሥራ አይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ያደጋ መከላከያ ይጠቀማሉ?:- በጥያቄ 911 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ብቻ የሚጠየቅ ሲሆን አማራጭ መልሶችም አዎን ኮድ 1 እና የለም ኮድ 2 ናቸው:: ስለዚህ ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 መከበቡን እንዲሁም ኮድ 2 ከተከበበ ወደ 915 ማለፉን ማረጋገጥ ይገባል::

914:-(ስም) የሚሠራውን የሥራ አይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ምውን አይነት የአደጋ መከላከያ ይጠቀማሉ?:- በጥያቄ 913 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ብቻ ሲጠየቅ አሞላሉም በጥያቄ በ912 መሰረት መከናወን ይኖርበታል::

915:-(ስም) በሚሠራው/በምትሰራው ሥራ ምክንያት ሊያጋጥሙት/ማት አሉ ብሎ ይሞላል/ትሞላለች?:- በጥያቄ 911 አዎን ለመለሱ የሚጠየቅ ሲሆን አማራጭ መልሶችም አዎን ኮድ 1 የለም ኮድ 2 እና አላውቅም ኮድ 3 ስለሆኑ ከተሰጡት ኮዶች ውስጥ አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡን ማየት ይገባል::

## ክፍል 10 ቤተሰብ/አሳዳጊ ላልሆነ ለሌላ ሰው በክፍያ (በገንዘብ ወይም በዓይነት) ወይም ያለክፍያ ተቀጥረው ስለሚሠሩ ልጆች

1001.ልጁ/ልጅቷ በአሁኑ ወቅት የሚሠራው ለማን ነው?:- ይህ ጥያቄ በቀጣይነት በዚህ ክልፍል መቅረብ ያለባቸውን ጥያቄዎች ለመጠየቅ የሚመለከታቸውን ልጆች ለመለየት ተስበ የቀረበ የማጣሪያ ጥያቄ ነው:: በመሆኑም በዚህ ክፍል ቀጣይ ጥያቄዎች ሊቀርብላቸው የሚገባ ልጆች ከቤተሰባቸው ውጭ ለሆነ ለሌላ ሰው/ድርጅት ይሰራሉ ተብሎ ኮድ 2 ከተሞላ

ብቻ መሆኑ መረጋገጥ አለበት:: ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ ጥያቄ ከተከበቡት ኮዶች እኳያ በይለፉ መመሪያ ወደ ተገቢው ጥያቄ መታለፉን ማረጋገጥም ይጠበቃል::

1002. <u>ልጁ/ልጅቷ ለሌላ ሰው የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ከአሠሪው/አሠሪዋ ጋር ያለው/ያላት ግንኙነት ምን ይመስላል?:-</u> ይህ ጥያቄ ከወላጅ/አሳዳጊ ውጭ ለሌላ ግለሰብ/ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ ልጆች ከአሰሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል የሚጠየቅበት ሲሆን ኮድ 1 እና 3 ከተከበበ ወደ 1004 መታለፋንና ኮድ 2 ከተከበበ ደግሞ ወደ ቀጣይ ጥያቄ መታለፉን መመልከት ያስፈልጋል:: ለዚህ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ መልስ የሚጠበቀው በጥያቄ 1001 ኮድ 2 ከተከበበ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ይህ ካልሆነ ግን ችግሩን ለኤዲቲንግ ተቆጣጣሪው በማሳየት በጋራ መፍትሄ መፈለግ ይኖርበታል::

1003. <u>ልጁ/ልጅቷ ከአሰሪው/ዋ ወይም ከቀጣሪው/ዋ ጋር ያለው/ያላት ግንኙነት መጥፎ ከሆነ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?:-</u> ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1002 ከአሰሪያቸው/ከቀጣሪያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት መጥፎ ነው ተብሎ ኮድ 2 ለተሞላላቸው የሚቀርብ ሲሆን ግንኙነታቸው መጥፎ የሆነበት ምክንያት ከተሰጡት አማራጮች አንፃር አዎን (ኮድ 1) ወይም የለም (ኮድ 2) መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1004.<u>ከሚከተሉት ጥቅማ ጥቀሞች ውስጥ ቀጣሪው የትኞቹን ለልጁ/ለልጅቷ ይሰጣል?</u> :- ይህ ጥያቄ ከቤተሰብ/አሳዳጊ ውጭ ለሌላ ሰው/ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ ልጆች ከአሰሪዎቻቸው ጥቅማ ጥቅም ማግኘት አለማግኘታቸውን ለማወቅ የቀረበ ጥያቄ ሲሆን የሚያገኙ ከሆነ ደግሞ ከተዘረዘሩት ጥቅማ ጥቀሞች ውስጥ የትኞቹን እንደሚያገኙ የሚጠየቅበት ነው:: በዚህም መሠረት ከተሰጡት አማራጭ መልሶች አንፃር አዎን (ኮድ 1) ወይም የለም (ኮድ 2) መሞላቱ መረጋገጥ አለበት:: ከአማራጮች መካከል አላውቅም ለሚለው ኮድ 1 ከተከበበ ለሌሎች አማራጮች ኮድ 1 ወይም 2 እንዲሞላ አይጠበቅም:: ከA እስከ I ካሉት አማራጮች መካከል ቢያንስ እንኳን ለአንዱ ኮድ 1 ከተከበበ በJ እና R አማራጮች ላይ የግድ ኮድ 2 መከበብ ስላለበት ይህ መረጋገጥ ይኖርበታል::

## <u>ክፍል 11፦ በምርታማ ሥራ የተሰማሩ ልጆች በመደበኛነት የሚኖሩባቸው ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጆቹ ያላቸው አመለካከት</u>

በዚህ ክፍል ውስጥ ከጥያቄ 1101 እስከ 1104 ድረስ ያሉ ጥያቄዎች የሚቀርቡት በምርታማ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ልጆች ሲሆን በጥያቄ 1001 ላይ በተገለፀው የይለፍ መመሪያ መሠረት ጥያቄዎች በትክክል መቅረባቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ለምሣሌ በጥያቄ 1001 ላይ ልጁ/ልጅቷ የሚሠራው/የምትሰራው በቤት ውስጥ ሠራተኛ ነው ተብሎ ኮድ 3 ተሞልቶ ከሆነ መታለፍ ያለበት ወደ ጥያቄ 1103 መሆን አለበት፤ ነገር ግን በክፍል 11 ከ1101 ጀምሮ ኮድ ተከቦ ቢገኝ ከክፍል 10 የይለፍ መመሪያ ጋር ስለሚቃረን ከኤዲቲንግ ተቆጣጣሪው ጋር በመሆን መፍትሄ መፈለግ ይገባል::

1101.<u>ልጁ/ልጅቷ ሥራ ቢተው/ብትተው በቤተሰቡ ላይ ምን ችግር ይመጣል?:-</u> በዚህ ጥያቄ በምርታማ ሥራ የተሰማሩ ልጆች ሥራ ቢተው በቤተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለው ችግር ምን እንደሆነ ለማወቅ የተፈለገ ሲሆን ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል የአንዱ እና ዋነኛው ምክንያት ኮድ መከበቡን መመልከት ያስፈልጋል::

1102A. <u>እንደ እርስዎ ፍላጐት ቢሆን (ልጁ/ልጅቷ) አሁን ምን ቢያደርግ/ብታደርግ ይመርጣሉ?:-</u> በዚህ ጥያቄ በምርታማ ሥራ የተሰማሩ ልጆችን አስመልክቶ ወላጆች/አሳዳሪዎች አሁን ምን አይነት ፍላጐት እንዳላቸው የሚጠየቁበት ሲሆን ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች መካከል የአንዱና ዋነኛው የአሁን የፍላጐታቸው አይነት ኮድ መከበቡን ማረጋገጥ ይገባል:: ምናልባት ከአንድ በላይ ኮድ ተከቦ ከተገኘ ሁኔታውን ለኤዲቲንግ ተቆጣጣሪው ማሳወቅ ያስፈልጋል::

1102B. <u>እንደ እርስዎ ፍላጐት ቢሆን (ልጁ/ልጅቷ) ወደ ፊት (ሲያድግ/ስታድግ) ምን ቢያደርግ/ብታደርግ ይመርጣሉ?:-</u> በዚህ ጥያቄም በምርታማ ሥራ የተሰማሩ ልጆች ወደፊት/ሲያድጉ ምን ቢያደርጉ እንደሚመርጡ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚጠይቁ ሲሆን ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል የአንዱና ዋነኛው የወደፊት ፍላጐታቸው ዓይነት ኮድ መከበቡን ማረጋገጥ ይገባል::

1103.<u>ልጁ/ልጅቷ ሥራ በማይሰራበት/በማትሰራበት ወቅት ምን ያደርጋል/ታደርጋለች?:-</u> በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩ ልጆች ሥራ በማይሰሩበት ወቅት ምን እንደሚያደርጉ በዚህ ጥያቄ የሚጠየቅ ሲሆን ከA እስከ E ለተዘረዘሩት አማራጮች ለእያንዳንዱ አዎን (ኮድ 1) ወይም የለም (ኮድ 2) መከበቡን መመልከት ያሻል::

1104.ልጁን/ልጅቷን ወደ ሥራ የገፋፋው/ት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?:- በዚህ ጥያቄ በምርታማ ሥራ የተሰማሩ ልጆችን ወደ ሥራ የገፋፋቸው ዋነኛ ምክንያት ምን እንደሆነ የሚጠየቅ ሲሆን ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል የአንዱና ዋነኛው ኮድ መከበቡን ማረጋገጥ ይገባል::

1105.ልጁ/ልጅቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ መሥራት የጀመረው/የጀመረችው በስንት አመቱ/አመቷ ነው?:- ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 801 ላይ ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ማለትም ያለክፍያ የቤት ውስጥ ስራ ለሰሩ እንዲሁም በጥያቄ 804 ላይ ኮድ 1 ለተከበበላቸው ነው:: ስለዚህም ምርታማ የሆነም ይሁን ያልሆነ ሥራ የሠሩ ልጆች ይህንን ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ ማከናወን የጀመሩት በስንት ዓመታቸው እንደሆነ ተጠይቆ ዕድሜአቸው በሙሉ ዓመት መሞላቱን መመልከት ይገባል:: እንደዚሁም በተሰጠው ካርድ ኮለም ውስጥ 02 እና በታች ተሞልቶ ከተገኘ ለኤዲቲንግ ተቆጣጣሪው ማሳየት የሚያስፈልግ ሲሆን ከ97 በላይ ተሞልቶ ከተገኘ ደግሞ ይህንን ሰርዞ በምትኩ 97 መሙላት ይገባል:: ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ክፍል የሚሞላው ዕድሜ ልጁ አሁን ከያዘው ዕድሜ ጋር እንዳይቃረን ማመሳከር ይጠበቃል::

1106.መረጃ ሰብሳቢ:- ስለ ልጁ/ልጅቷ መልስ የሰጠው የቤተሰብ አባል ተራ ቁጥር ከቅጽ 1 ዓምድ 12 የሚወሰድ:: ይህ ጥያቄ መረጃ ሰብሳቢው ራሱ ወደኋላ ሂዶ ለቀረበው ጥያቄ መልስ የሰጠውን የቤተሰብ አባል ተራ ቁጥር ከቅጽ 1 ዓምድ 12 ወስዶ የሚሞላበት ሲሆን በትክክል ስለመሞላቱ ቅጽ 1ን በመመልከት የማይቃረን መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

# ምዕራፍ VI የቅፅ 3 የልጆች የሥራ ስምሪት መጠይቅን ማረም

## ክፍል 12 ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆች የትምህርት፣ የሥራ ሁኔታና በሥራ ላይ ስለሚደርሱ ጉዳቶችና ህመሞች

ማስታወሻ:- ቅጽ 3 በተለያየ ምክንያት ካልተሞላ ዕድሜአቸው ከ5-9 ለሆኑ ወይም ልጆች ሳይገኙ በመቅረታቸው በቅፅ 3 ገፅ 6 ባለው ሠንጠረዥ በቀኝ አናት ላይ ሳጥን በመስራት በውስጡ ኮድ 2 ይሞላል:: ቅፅ 3 ከተሞላ ግን በሳጥኑ ውስጥ ኮድ 1 ይሞላል::

1201. (የልጁ/ጅቷ ስም) በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት እየተከታተልክ/ሽ ነው? ምን ዓይነት ትምህርት? በዚህ ጥያቄ ዕድሜአቸው ከ10-17 የሆኑ ልጆች ስለትምህርት ሁኔታ የሚጠየቁበት ነው:: ስለዚህ ከተሰጡት አራት አማራጭ ኮዶች ተጠያቂዎች በሚሰጡት መልስ መሠረት አንዱ መከበቡን ማረጋገጥና መልስ መስጠት ሲገባው ካልተሰጠ ግን ለተቆጣጣሪው ችግሩን በማሳየት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲሰጥ ማድረግ ተገቢ ነው::

1202. (የልጁ/ጅቷ ስም) አሁን የምትከታተለው/ይው የክፍል ወይም የትምህርት ደረጃ ስንተኛ ነው?:- ከላይ በጥያቄ 1201 ሲጠየቁ አዎን ብለው ኮድ 1 ለተከበበላቸው ይህ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል:: ከ1ኛ-12ኛ ክፍል ለሚከታተሉ ያሉበት ክፈለ እንደ ኮድ ይወሠድላቸዋለ ከ12ኛ ክፍል በላይ ከሆኑ ኮደ 13 ሲሞላላቸው ከዚህ ጥያቄ በፊት በቅጽ 1 ዓምድ 20 ላይ የተሞላላቸው ጋር ሲታይ በአንድ ክፍል ከፍ ሊል ይችላል::

1203. (የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት ትምህርት ተከታትለህ/ሽ ነበር?:- በዚህ ጥያቄ ጥየቱ በሚካሄድበት ሣምንት በተራ ቁጥር 1201 መደበኛ ትምህርት የሚከታተሉ ሆነው ኮድ 1 ለተከበበላቸውና በተራ ቁጥር 1202 ላይ የትምህርት ደረጃ በሣጥኑ ውስጥ ለተሞላላቸው ይህ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል:: በተጨማሪም በጥያቄ 1201 ላይ ኮድ 3 የተሞላላቸው ይህንን ጥያቄ መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1204. (የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት ስልጠና ተከታተለህ/ሽ ነበር?:- ይህ ጥያቄ የሚያተኩረው ልጆች ከትምህርት በተጨማሪ ወይም ከትምህርት ውጭ የሙ ያ ስለጠና እየተከታተለ መሆኑን ለማወቅ ነው ስለዚህ በተራ ቁጥር 1203 ትምህርት አልተከታተልኩም ብለው ኮደ 5 ለተከበበላቸው ብቻ የሚቀርብ ጥያቄ ነው::

1205. (የልጁ/ጅቷ ስም) ከዚህ ቀደም መደበኛ ትምህርት ተምረሀ/ሽ ነበር ወይም ስልጠና ተከታትለህ/ሽ ነበር? ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በጥያቄ 1201 ኮድ 4 የተከበበላቸው እና ለጥያቄ 1204 ላይ ኮድ 4 የተከበበላቸው የሚመለከት ነው:: በዚህ መሠረት ተጠይቆ ከተሰጡ አማራጮች አንዱ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ለዚህ ጥያቄ ኮደ 4 የተሞላላቸው ልጆች ወደ ጥያቄ 1207 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1206. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) መደበኛ ትምህርት ያልተከታተልከበት/ሽበት ወይም ትምህርት ያቋረጥከበት/ሽበት ወይም ስልጠና ያልወሰድከበት/ሽበት ምክንያት ምንድነው?</u> ከላይ በጥያቄ 1205 ከኮድ-3 የመለሱትን ማለትም ትምህርት ያቋረጡትኝ፡ መደበኛ ያለሆነ ትምህርት ብቻ የሚማሩትንና ምንም የማይማሩትን የሚመለከት ነው:: ስለዚህ መልሱ በትክክል መሠጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህንን ጥያቄ የተጠየቁ ልጆች በሙሉ ቀጣዩን ጥያቄ 1207 ሳይጠየቁ ወደ 1208 ማለፋቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው::

1207 <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት ለምን አልተማርከም/ሽም?:-</u> ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1205 ኮድ 4 የተከበበላቸውን ብቻ የሚመለከት ነው:: እነዚህ ልጆች በዚህ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት በመማር ላይ የሚገኙትን ሲሆን በጥናቱ ሣምንት ብቻ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከትምህርት ቤት የቀሩ ናቸው:: ስለዚህ አስፈላጊው መልስ መከበቡን ማረጋጥ ያስፈልጋል::

1208. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፉት 7 ቀናት ያከናወንካቸው/ሻቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?</u> ይህ ጥያቄ ልጆች ባለፈው ሣምንት ሙሉ ወይም ጊዜአቸውን እንዴት እንዳሣለፉ የሚመለከት ነው:: ስለዚህ በጥያቄ 1203 ከኮድ 1-3 በጥያቄ 1204 ከኮድ 1-3 በጥያቄ 1206 ከኮድ 1-15 በይለፍ የመጡትንና በጥያቄ 1207 1-6 ለተከበበላቸው በትክክል መልስ መስጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1209. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በትላንትናው ዕለት በሰራህባቸው/ሽባቸው በሁሉም ሥራዎች ለስንት ሰዓት ሰርተሃል/ሻል?</u> በዚህ ጥያቄ ባለፈው ቀን ልጆቹ የሠሩዋቸውን ጠቅላላ የሥራ ሰዓት መጠን ይሞላል:: ይህ ጥያቄ የሚመለከተው ቀደም ብለው ባለው ቀን ወይም በትላንትናው ቀን የሠሩት የሥራ ሠዓት ሲሆን ይህም በምርታማ ተግባር በመሥራት ያሣለፉትንና የቤት ውስጥ ሥራ የሠሩበትን የሥራ ሰዓት አንድ ላይ በመደመር ነው:: በዚህ መሠረት በጥያቄ 1208 ከኮድ 1-3 ለተከበበላቸው በተሰጠው ሣጥን ውስጥ የሥራ ሰዓት ድምር መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1210. <u>(የማጣሪያ ጥያቄ)</u> ይህ ጥያቄ ልጆች ባለፈው ሣምንት ትምህርት/ሥልጠና ተከታትለው እንደሆነ የማጣሪያ ጥያቄ በመሆኑ መረጃ ሠብሳቢው የተጠቀሱትን ጥያቄዎች አገናዝቦ በትክክል መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1211. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራህ/ሽ ትምህርትህን/ሽን በደንብ እንዳትከታተል/ይ አድርጓል?:-</u> ይህ ጥያቄ ሥራ እየሠሩ ከፊል ጊዜያቸው በትምህርት ላይ የሚያሣልፉ ልጆችን ይመለከታል:: በጥያቄ 1210 ላይ ኮድ 1 ለተከበበላቸው ብቻ መልስ መስጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1212. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራውን የምትሠራው/ሪው ለማነው?:-</u> ይህ ጥያቄ የሚጠየቁት ልጆች ጥያቄ 1211 የተጠየቁትና ጥያቄ 1210 ኮዴ 2 የተከበበላቸው ናቸው:: ለዚህ ጥያቄ 5 አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል ከነዚህ ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥና ኮዴ 1 የተሞላላቸው ልጆች ወደ 1225፡ ኮዴ 3 እና 4 የተከበበላቸው ወደ 1214 እና ኮዴ 5 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ 1222 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ነገር ግን ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ጥያቄ መጠየቃቸው ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

1213. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) አብዛኛውን ጊዜ ትርፍ ሰዓት ትሰራለህ/ሪያለሽ? ከሠራህ/ሽ በክፍያ ነው?:-</u> ይህ ጥያቄ ከቤተሰብ ውጭ ለሌላ ግለሰብ/ድርጅት በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚሠሩትን ይመለከታል:: በጥያቄ 1212 ኮድ 2 ለተከበበላቸው ብቻ የተጠየቀ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1214. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሰሪህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ግንኙነት እንዴት ነው?:-</u> ልጆች ተቀጥረው በሚሰሩበት ወቅት ከአሠሪያቸው ጋር ጥሩም ሆነ መጥፎ ግንኙነት ሊመሠርቱ ይችላሉ ይህንን ሁኔታ ለማወቅ እንዲቻል የቀረበ ጥያቄ ስለሆነ በጥያቄ 1212 ከኮድ 3 እና 4 በጥያቄ 1213 ከኮድ 1-3 ለተከበበላቸው በትክክል ተጠይቆ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1215. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሰሪህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ግንኙነት መጥፎ የሆነበት ዋናው ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?</u> ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1214 ከአሠሪያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት መጥፎ ነው ብለው ለመለሱ ግንኙነቱ መጥፎ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅ የሚያስችል ነው:: በጥያቄ 1214 ላይ ኮድ 2 ለተከበበላቸውና ከA-G ድረስ ለተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች አዎን ወይም የለም በሚለው ከሁለቱ በአንዱ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1216. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በአሁኑ ወቅት በክፍያ የምትሰራ/ሪ ከሆነ በስንት ጊዜ ነው ክፍያ የሚሰጥህ/ሽ?</u>

ይህ ጥያቄ ከቤተሰብ ውጭ ለሌላ ግለሰብ/ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩትን የሚመለከት ይሆናል:: በጥያቄ 1214 ከኮድ 1 3 እና ጥያቄ 1215ን የተጠየቁትን ይህንንም ጥያቄ መጠየቁን ማረጋገጥ:: በተጨማሪ ኮዱ 9 የተከበበላቸው ወደ 1225 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ተገቢነት አለው::

1217. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በአካባቢው ካለው የአከፋፈል ሁኔታ አንፃር የተመጣጠነ ክፍያ ታገኛለህ/ሽ?</u>
ጥያቄው የሚመለከተው በ1216 ላይ ከኮዱ 1-8 የተከበበላቸውን ነው:: ስለዚህ ለዚህ ጥያቄ ሁለት አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል:: ከሁለቱ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ በቂ ነው::

1218. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በቅርቡ (የመጨረሻው) በአሰሪህ/ሽ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለህ/ሽ ክፍያ ምን ያህል ብር ነው?</u> ይህ ጥያቄ ልጆቹ ለሚሠሩት ሥራ በቅርቡ በገንዘብ የተከፈላቸውን ክፍያ መጠን የሚሞላበት ሲሆን በጥያቄ 1217

ኮድ 1 እና 2 ለተከበበላቸው ብቻ የሚሞላ ነው:: እንዲሁም በዚህ ጥያቄ ካርዱ ኮለሞች ሲኖሩ በሁሉም ካርዱ ኮለሞች ውስጥ ቁጥር መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ 64 ብቻ ተፅፎ ቢመጣ ከፊቱ ሁለት ዜሮዎች መሙላት ያስፈልጋል::

1219. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በቅርቡ (የመጨረሻው) በዓይነት ወይም በዕቃ የተከፈለህ/ሽ መጠን በብር ተገምቶ ምን ያህል ነው?</u>
ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1218 ከተገለፀው ጋር ተመሣሣይነት ያለው ሲሆን ልዩነቱ አከፋፈሉ በዓይነት ወይም በዕቃ መሆኑ ነው:: ስለዚህ በዓይነት የተቀበሉት ወደ ገንዘብ ተለውጦ በተሠጠው ሣጥን ውስጥ በትክክል መመዝገቡን ማየት ያስፈልጋል:: አሞላሉም ልክ ከላይ ለጥያቄ 1218 በተገለፀው መሠረት መሆን አለበት::

1220. <u>በገንዘብና በዓይነት የተከፈለ ክፍያ ድምር</u>
ከላይ በጥያቄ 1218 በገንዘብ የተገኘን ክፍያ እና በጥያቄ 1219 በዓይነት ወይም በዕቃ የተገኘ ክፍያ መረጃ ሰብሳቢው በትክክል ደምሮ በተሰጠው ካርድ ኮለም መሙላቱን ማረጋገጥ:: በተለያየ ምክንያት ሳይከፈላቸው ቀርቶ ኮድ 9998 በ1218 እና በ1219 ላይ የተሞላ ከሆነ በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሞላው 9998 ብቻ መሆኑንና የሁለቱ ድምር አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1221. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከተቀበልከው/ሽው ገንዘብ ከፊሉን ወይም ሙሉውን ለቤተሰብ ወይም ለአሳዳጊህ/ሽ ወይም ለሌላ ለምትኖርባቸው ዘመዶችህ/ሽ ትሰጣለህ/ጫለሽ?:-</u>
ይህ ጥያቄ ልጆቹ ሠርተው የሚያገኙትን ገንዘብ የት እንደሚያውሉትና ለምን እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ የሚያስችል ጥያቄ ነው:: ለዚህ ጥያቄ ሰባት አማራጭ መልቦች ተሰጥተዋል:: ስለዚህ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ እና ኮዱ 1፣ 2 እና 6 የተሞላላቸው ወደ ጥያቄ 1225 መሸጋገራቸውንና ከነዚህ ውጪ ኮዱ የተሞላላቸው ማለትም ኮድ 3፣ 4፣ 5 እና 7 ቀጣዩን ጥያቄ መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

1222. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ሠርተህ/ሽ ካገኘኸው/ሽው ገንዘብ ከፊሉን ትቆጥባለህ/ቢያለሽ? :-</u> ይህንን ጥያቄ የሚጠየቁት ልጆች ከላይ ለጥያቄ 1221 ኮዱ 3፣ 4፣ 5 እና 7 የተሞላላቸው ጆኖች ናቸው:: ለዚህ ጥያቄ ሦስት አማራጮች ተሰጥተዋል ከነዚህ ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ኮድ 3 የተከበበላቸው ወደ ጥያቄ 1225 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1223. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) አብዛኛውን ጊዜ የምትቆጥበው/ቢው እንዴት ነው?:-</u>ይህ ጥያቄ ከላይ 1222 ልጆቹ ከሚያገኙት ክፍያ ከፊሉን በቋሚነት ወይም አልፎ አልፎ እንደሚቆጠቡ ግልፀው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ለተከበበላቸው እንዴት እንደሚቆጠቡ ለማወቅ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሆነ ከተሰጡት 4 አማራጮች መልስ ውስጥ አንዱ ብቻ በትክክል መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1232 (የማጣሪያ ጥያቄ) ልጆች ባለፈው ሳምንት በምርታማ ሥራ መሠማራት/አለመሠማራታቸውን ከጥያቄ 1208 ይጣራል::- ይህ ጥያቄ የማጣሪያ ጥያቄ ነው:: ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢዎች በይለፍ ደንቡ መሠረት ከጥያቄ 1208 አጣርተው በትክክል ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ማለት በዚህ ጥያቄ ኮድ 1 የተከበበላቸው ማለትም 1208 ላይ ኮድ 1 ወይም 2 የተሞላላቸው መሆናቸውን እና ኮድ የተሞላላቸው ደግሞ በጥያቄ 1208 ላይ ከኮድ 3 -5 የተሞላላቸው መሆናቸውንና ወደ ጥያቄ 1239 ማለፋቸው ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው::

1233. (የልጁ/ጅቷ ስም) በመስሪያ ቦታህ/ሽ ወይም በግል ስራህ/ሽ አካባቢ ማንኛውም የእጅ መሣሪያ/ማሽን ታንቀሳቅሳለህ/ሻለሽ?:- አንዳንድ ልጆች ጉልበታቸው ከሚጠይቀው በላይ የእጅ መሣሪያ ለምሳሌ መጥረቢያ፣ ዶማ:- ማረሻ፣ አካፋ በመሣሠሉት መሣሪያዎች ሥራ መሥራትን ይመለከታል በጥያቄ 1232 ላይ ኮድ 1 ማለትም (በጥያቄ 1208 ኮድ 1 ወይም 2) ለተከበበላቸው በትክክል የይለፍ ደንቡን ጠብቆ መሠራቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1234. (የልጁ/ጅቷ ስም) በሥራ ላይ እያለህ/ሽ የሚከተሉትን የጉዳት መከላከያዎች ትጠቀማለህ /ትጠቀሚያለሽ? የምትጠቀም/የምትጠቀሚ ከሆነ ምን ዓይነት የአደጋ/የጉዳት መከላከያ ትጠቀማለህ/ትጠቀሚያለሽ?:-የዚህ ጥያቄ አላማ በምርታማ ሥራ ላይ የተሠማሩ ልጆች የጉዳት ወይም የአደጋ መከላከያዎችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህ መሠረት በጥያቄ 1233 ላይ አዎን ወይም የለም ብለው ኮድ 1 ወይም 2 ለተከበበላቸው ከA-G ላሉት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው ተጠይቆ አዎን ወይም የለም ከሁለት አንዱ መከበቡን ማረጋጥ ያስፈልጋል::

1235. (የልጁ/ጅቷ ስም) የምትሠራውን/ሪውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች የአደጋ መከላከያ ያደርጋሉ/ይጠቀማሉ?:- ይህ ጥያቄ ልጆቹ የሚሠሩትን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች የአደጋ መከላከያ መጠቀም አለመጠቀማቸውን በመጠየቅ የአደጋ መከላከያ አጠቃቀምን በተመለከተ ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ንፅፅር ለማየት የሚረዳ ሲሆን በትክክል መጠየቁን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለዚህ ጥያቄ ኮድ 2 የተከበበላቸው ልጆች ወደ ጥያቄ 1237 ማለፋቸው ይረጋገጥ::

1236. (የልጁ/ጅቷ ስም) የምትሰራውን/ሪውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት የአደጋ/የጉዳት መከላከያ ያደርጋሉ/ይጠቀማሉ?:- እዚህ ጥያቄ ላይ ልጆቹ የሚሠሩትን የሥራ ዓይነት ሌሎች ሰዎች በጥያቄው ውስጥ የተዘረዘሩትን የጉዳት ወይም የአደጋ መከላከያዎች ይጠቀሙ እንደሆነ ከላይ በጥያቄ 1235 ተጠይቀው አዎን ብለው ኮድ 1 ለተከበበላቸው ብቻ ተጠይቆ አዎን ወይም የለም ከሁለት አንዱ መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

1237. (የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራህ/ሽ ለጤና መታወክ ወይም ለአካል ጉዳት፣ ለህመም ወይም ለሌላ ጠንከር ላለ የጠና ችግር የሚያስከትልብህ/ሽ ይመስልሃል/ሻል?:- የዚህ ጥያቄ አላማው አንዳንድ ልጆች የሚሠሩት ሥራ የሚያሥከትልባቸውን የጉዳት/ህመም ሁኔታ ስለማይገነዘቡ ለጉዳት/ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል:: ስለዚህ ጉዳት ወይም አደጋ እንደሚያጋጥማቸውና እንደማያጋጥማቸው ያላቸው ግንዛቤ ተጠይቆ የተሞላ ስለሆነ ይታይ:: በተጨማሪም ከተሰጡት ሦስት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥም ያስፈልጋል::

1238. (የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሁኑ ሥራህ/ሽ ጋር የተያያዘ ችግር አጋጥሞህ/ሽ ያውቃል?:-ይህ ጥያቄ ልጆቹ የሚሠሩት ሥራ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ዓይነት ችግር (የአካል ጉዳት/ህመም፣ የገንዘብ ማጣት፣ አለመርካት፣ ... ወዘተ) የሚመለከት ነው:: በዚህ ጥያቄ የቤተሰቡ አባላት የሆኑ ልጆች በሥራቸው ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው እንደሆነ ተጠይቆ ከተሰጡት ሁለት አማራጮች አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1239. (የማጣሪያ ጥያቄ) ይህ ጥያቄ መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጪውን ሳይጠይቅ ጥያቄ 1201ን፣ 1203ን ፣ 1204 እና 1208ን በማየት ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ በሥራም ሆነ በትምርት/በስልጠና ተሳትፎ/ፏ እንደሆነ የሚያጣራበት ነው:-ይህ ጥያቄ የማጣሪያ ጥያቄ ሲሆን መረጃ ሠብሳቢው በትክክል ማጣሪያዎቹን አይቶ ትክክለኛውን ኮድ መሙላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም በዚህ ጥያቄ ኮድ 1 የተከበበላቸው ከሆነ ወደ 1241 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

1240. (የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ምንም ያልሠራህበት/ሽበት ወይም ትምህርት/ስልጠና ያልተከታተልክበት ሽበት ምክንያት ምንድነው?:-ባለፈው ሣምንት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ምንም ሥራ ካልሠሩ ወይም ትምህርት ላልተማሩና ወይም ሥልጠና ላልወሰዱ ማለትም በሁለቱም ካልተሠማሩ ያልተሠማሩበት ምክንያት ምን እነደሆነ የሚጠየቅበት ነው:: ይህ ጥያቄ የሚጠየቅላቸው 1239 ላይ ኮድ 2 የተከበበላቸው ናቸው:: በመሆኑም ከተሰጡት 7 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ ብቻ መከበቡን እና ኮድ 7 ተሞልቶ በሌላ የተገለፀው ከኮድ 1 እስከ 6 ካሉት ጋር የሚያቀራርብ ከሆነ ማስተካከል ተገቢ ነው:: ስለዚህ ከተቆጣጣሪዎቹ ጋር በማማከር የሚሰራ ይሆናል::

1241. (የልጁ/ጅቷ ስም) እንደ አንተ/ቺ ፍላጎት ቢሆን አሁን ምን ማድረግ ትፈልጋለህ/ሽ?:-በዚህ ጥያቄ ልጆች እንደሚፈልጉት ወይም እንደምርጫቸው ቢሆን አሁን በቅርቡ ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ ተጠይቀዋል:: በዚህ ምክንያት አንድ ዋና መልስ ብቻ ስጥተዋል ከኮድ 01-10 ከተሰጡት መልሶች አንዱ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::

1242. (የልጁ/ጅቷ ስም) እንደ አንተ/ቺ ፍላጎት ቢሆን ወደፊት ስታድግ/ጊ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ/ሽ?:- ይህ ጥያቄ ከላይ ከተገለፀው ጋር ተመሣሣይነት ስለአለው አማራጭ መልሶቹን ከጥያቄ 1241 በተዘረዘሩት መሠረት ሆኖ ለጥያቄው መልስ አሰጣጡ ግን ይለያያል ስለዚህ በዚህ ጥያቄ የሚሠጠው መልስ ወደፊት የረጅም ጊዜ ፍላጎታቸውን የሚጠየቁበት ስለሆነ ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን ተጠይቀው አንድ መልስ መከበቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

# የ1993 የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት <u>ተጨማሪ</u> የእርማት መመሪያ

## I <u>አባሪ መጠይቅን ማረም</u>

የአካባቢ መለያ:- ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ/ወረዳ፣ ቀበሌ(ገ/ማ) የቆጠራ ቦታ እና የተመረጠው ቤተሰብ ምርጫ ተ.ቁ ከቅጽ 1 በትክክል መወራረሱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

<u>ከቤተሰቡ ኃላፊ የሚጠየቁ ተጨማሪ ጥያቄዎች</u>

ጥያቄ 71 <u>ከቤተሰቡ ኃላፊ/ባለቤት ልጆች መካከል ዕድሜአቸው 5-17 ዓመት የሆኑ ሌላ ቦታ የሚኖሩ ልጆች አሉ?</u>
በዚህ ዓምድ ከቤተሰቡ ኃላፊ/ባለቤት ልጆች መካከል ዕድሜአቸው 5-17 ዓመት የሆኑ ሌላ ቦታ የሚኖሩ ልጆች ያላቸው ከሆነ ኮድ 1 ሌላ ቦታ የሚኖር ልጅ ከሌላቸው ወይም ሌላ ቦታ የሚኖር ልጅ ቢኖራቸውም ዕድሜአቸው 5-17 ካልሆነ ኮድ 2 ይከበባል:: ኮድ 2 የተከበበ ከሆነ መጠይቁ የሚያበቃ ስለሆነ ቀጣይ አምዶች አይጠየቁም:: ኮድ 1 የተከበበ ከሆነ ግን የሚቀጥሉት ዓምዶች መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ጥያቄ 72:- <u>ከቤተሰቡ ኃላፊ/ባለቤት መካከል ስንት ወንድ እና ስንት ሴት ልጆች ሌላ ቦታ ይኖራሉ?</u>
በዚህ ዓምድ ሌላ ቦታ የሚኖር ልጅ አለኝ ብለው በጥያቄ 71 ላይ ኮድ 1 የተከበበ ከሆነ ስንት ወንዶች ልጆችና ስንት ሴት ልጆች እንደአላቸው የሚጠየቅበት ነው:: ስለዚህ ለወንዶች ልጆች ብዛት መፃፊያ ሁለት ካርድ ኮለም እንዲሁም ለሴት ልጆች ብዛት መፃፊያ ሁለት ካርድ ኮለም የተተወ ሲሆን በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ሌላ ቦታ የሚኖር ሴት ልጅ ወይም ወንድ ልጅ የሌላቸው ከሆነ በተሰጠው ካርድ ኮለም «00» ይሞላል::

<u>ከቤተሰቡ ኃላፊ/ባለቤት ልጆች መካከል ሌላ ቦታ ስለሚኖሩ ልጆች አንዳንድ ጥያቄዎች</u>

በጥያቄ 72 የተመዘገቡት ሌላ ቦታ የሚኖሩ ዕድሜአቸው 5-17 በሆኑ ልጆች ብዛት መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ልጅ ከጥያቄ 73-76 የሚጠየቅበት ነው:: በዓምድ 72 የተሞላው የወንዶችና የሴቶች ልጆች ድምር እና በጥያቄ 73-76 መረጃ የተሞላላቸው ልጆች ብዛት መጣጣም አለበት::

<u>ጥያቄ 73:- የ______ ዕድሜ ስንት ነው? (ዕድሜ በሙሉ ዓመት)</u> በስተቀኝ በተዘረዘረው መሠረት ሌላ ቦታ ከሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች ልጆች መካከል ትልቅ ከሆነው በመጀመር ለእያንዳንዳቸው ዕድሜአቸው ስንት እነደሆነ የሚጠየቅበት ነው:: ስለዚህ በተሰጡት ሁለት ካርድ ኮለሞች ትክክለኛው መልስ መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ሲሆን ዕድሜ ከ17 መብለጥ የለበትም፣ ከ5ም ማነስ የለበትም:: የልጆች ዕድሜ ከወላጆቻቸው መብለጥ የለበትም::

<u>ጥያቄ 74:- የ______ ፆታ ምንድን ነው?</u>
ሌላ ቦታ ከሚኖሩ ልጆች ትልቅ ከሆነው በመጀመር የሁሉም ልጆች ፆታ አንድ በአንድ የሚጠየቅበት ነው:: ስለዚህ ወንድ ከሆነ ኮድ 1 ሴት ከሆነች ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል:: እንዲሁም በዓምድ 72 ከተሞላው ሌላ ቦታ የሚኖሩ ወንዶች ልጆች ብዛትና ሴቶች ልጆች ብዛት ከዚህ ዓምድ ጋር ማገናዘብና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::
<u>ጥያቄ 75</u> ___ከማን ጋር ነው ሌላ ቦታ የሚኖረው::
በዚህ ዓምድ ሌላ ቦታ ከሚኖሩ ልጆች ከትልቁ በመጀመር እያንዳንዱ ልጅ ከማን ጋር እንደሚኖር/ትኖር የሚጠየቅበት ነው:: አማራጮች መልሶችም ከኮድ 1-7 በጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል:: ስለዚህ ለእያንዳንዱ ልጅ አስፈላጊው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::
ጥያቄ 76:- <u>የ___ አኗኗር እንዴት ነው?</u> በዚህ ዓምድ ሌላ ቦታ የሚኖሩ ልጆች የአኗኗር ሁኔታ የሚጠየቅበት ሲሆን ከትልቁ ልጅ በመጀመር ለእያንዳንዱ ልጅ አስፈላጊው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: አማራጭ መልሶችም በዓምድ ከኮድ 1-4 ተዘርዝረዋል::
በመጨረሻም ከዓምድ 73-76 መረጃ የተሞላላቸው ልጆች ብዛትና በዓምድ 72 የተመዘገቡት የወንዶችና ሴቶች ልጆች ብዛት ድምር ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል::

## <u>II</u> <u>ተጨማሪ ኮድ እና ማብራሪያ</u>

<u>ዓምድ 34</u>
ኮድ=7 በየ 15 ቀኑ (አዲስ)
ኮድ=8 ሌሎች

<u>ዓምድ 62 የቤቱ ጣሪያ የተሰራበት ዓይነት</u>
በኮድ 6= ሌላ (ይገለጽ) ሥር የተዘረዘሩት
-የስንዴ ቃርሚያ/ቅጠል ከሆነ ወይም ቀርከሃና ሣር ከሆነ ወይም ፕላስቲክና ሣር ከሆነ ኮድ 3 (ሣር) ይሞላ
-እንጨት፣አፈርና ሣር ከሆነ ኮድ 4 (እንጨትና አፈር) ይሞላል::

<u>ዓምድ 67</u> : የሚጠቀሙት ማገዶ አይነት
-የማሽላ/የበቆሎ አገዳ ከሆነ ኮድ 5 (እንጨት/ከሰል፣ ኩበት)ይሞላል::

<u>ጥያቄ 604</u>

ኮድ 4=ምንም አልሰራም/ችም ወይም ልጅ ስለሆነ/ነች (አዲስ)

ኮድ 5= ሌሎች

<u>ጥያቄ 605</u>

ኮድ 0= ከወላጅ ጋር ለመኖር (አዲስ)

<u>ጥያቄ 705</u>

ኮድ 15=ዕድሜው ለትምህርት ስላልደረሰ ወይም ልጅ ስለሆነ(ች)(አዲስ)

ኮድ 16= ሌሎች

<u>ጥያቄ 903</u>

ለዚህ ጥያቄ የተሞላው የድርጅት ዓይነት <u>ለራስ ቤተሰብ ያለ ክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ</u> የሚሰራበት ቤተሰብ የሚያመለክት ከሆነ ኮድ 960 ይሞላል:: በዚህ ዓምድ የተሞላው መልስ በጥያቄ 904 ላይ ከተሞላው ጋር ማስተያየት ያስፈልጋል::

<u>ጥያቄ 904</u>

ለዚህ ጥያቄ የተሞላው የሥራ ዓይነት በቤት ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎች (ለምሳሌ ውሃ መቅዳት፣ እንጨት መልቀም...) በሚሆንበት ወቅት ሥራው የተሰራው በቅጥር ከሆነ እንደተለመደው ኮድ 913 ይሞላል:: ሥራው የተሰራው ለራስ ቤተሰብ ያለክፍያ ምርታማ ያልሆነ) ከሆነ::

ምግብ ማብሰል ኮድ 941

ውሃ ቅዳት ኮድ 942

እንጨት መልቀም ኮድ 943

ሌላ ያለ ክፍያ የቤትውስጥ ሥራ 944 ይሞላል

<u>ማስታወሻ:-</u> ልጁ/ልጅቷ የሚሰራው/የምትሠራው ሥራ የቤት ውስጥ ሥራ ሆኖ ነገር ግን በቅጥር ወይም ያለክፍያ ለራስ ቤተሰብ መሆኑን ተገልጾ ካልተጻፈ ልጁን/ልጅቷን ከኃላፊው ጋር ያላውን/ትን ዝምድና በማየት ለመለየት ይሞከር፣ ይህን በማድረግ መለየት ካልተቻለ ኮድ <u>950</u> ይሞላል:

<u>ጥያቄ 914</u>

በዚህ አምድ እንደ አደጋ መከላከያ በፊደል 'F' ሌላ(ይገለጽ) ሥር ሊዘረዘሩ የሚችሉ <u>ለምሳሌ:</u>

-ቱታ፣ በርባሶ ጫማ፣ የአሲድ መከላከያ ልብስ፣ እና ሌሎችም ከተገኙ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር በዚህ ኮድ ሊካተቱ ይችላሉ ነገር ግን እንደ የሰሌን ባርኔጣ፣ ጃንጥላ፣ የዝናብ መከላከያ ላስቲክ ተሞልቶ ከመጣ ይህን በመሰረዝ በስተቀኝ የሚገኘውን ኮደ 2 ማክበብ ያስፈልጋል::

<u>ጥያቄ 1004</u>

በዚህ ጥያቄ ከፊደል A-J ለተዘረዘሩት ጥቅማ ጥቅሞች በአንዱም እንኳ ኮድ 1 ወይም 2 ሳይከበብ ነገር ግን በፍደል K አላውቅም ለሚለው ኮድ 1 ከተከበበ፣ ከፊደል A-J በእያንዳንዱ ፊደል ትይዩ ኮድ 3 በመጻፍ ማክበብ ያስፈልጋል::

በሌላ በኩል ከፊደል A-J ለተዘረዘሩት ጥቅማ ጥቅሞች ለተወሰኑት (ቢያንስ በአንዱ) ኮድ 1 ወይም 2 ተከቦ ለሌሎቹ ምንም ሳይከበብ ቢቀር ምንም ባልተከበበላቸው ፊደሎች ትይዩ ኮድ 9 ተጽፎ ይከበባል::

<u>ጥያቄ 1102A</u>

ኮድ 10= ትዳር እንዲመሰርት/እንድትመሰርት (አዲስ)

ኮድ 11 = ሌሎች

<u>ጥያቄ 1102B</u>

ኮድ 10= ትዳር እንድትመሰርት/እንዲመሰርት (አዲስ)

ኮድ 11 = ሌሎች

<u>ጥያቄ 1104</u>

ኮድ 7= ራሱን ለመርዳት (አዲስ)

ኮድ 8 = ሌሎች

<u>ጥያቄ 1206</u>

ኮድ 15 = መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (አዲስ)

ኮድ 16= ሌሎች

<u>ጥያቄ 1226</u>

ኮድ 6= ትምህርት ከመማር ስለአገደኝ/ለትምህርት ስለማይመች(አዲስ)

ኮድ 7 = ሌሎች

<u>ጥያቄ 1236</u>

ከላይ ለጥያቄ 914 ስተሰጠው ማብራሪያ መሠረት::

<u>ጥያቄ 1241</u>

ኮድ 10= ትዳርእንድትመሰርት/እዲመሰርት (አዲስ)

ኮድ 11=ሌሎች

<u>ማስታወሻ:-</u> በጽሑፍም ሆነ በኮድ ሳይሞሉ ባዶ የመጡ ጥያቄዎች ካጋጠሙ ከተቆጣጣሪዎች ጋር በመመካከር ሌሎች ዓምዶች ላይ ያሉ መረጃዎችን በመጠቀም መሙላት ይገባል በዚህ መንገድ መፍትሄ መስጠት ካልተቻለ ከተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር ኮድ 9፣ 99 ወይም 999 ይሞላል::